https://t.me/customsclearingagents ..... For More



ረቂቅ የአምራች ኢንዱስትሪ ፖሊሲ

ሰኔ 2014 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

https://t.me/customsclearingagents ..... For More

ማውጫ

1. መግቢያ 1
2. የፖሊሲው አስፈላጊነት 2
3. የፖሊሲው ርዕይ፣ ግብ፣ ዓላማዎችና መርሆች 3
4. የፖሊሲው ወሰን 5
5. የፖሊሲ ዋና ዋና ጉዳዮች 5
   - 5.1. የማክሮ ኢኮኖሚና የቢዝነስ ሥነ-ምህዳር 6
   - 5.2. ፋይናንስ 15
   - 5.3. የሰው ሃይል ልማት እና አስተዳዳር 19
   - 5.4. ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን 22
   - 5.5. ምርት ልማትና ተወዳዳሪነት 26
   - 5.6. የአካባቢ እና ማህበራዊ አካታችነትና ዘላቂነት 32
6. የፖሊሲው አፈፃፀም ማዕቀፍ 35
7. ፖሊሲውን የማስፈፀም ኃላፊነት ያለባቸው ተቋማት 35
8. የፖሊሲ ክትትል፣ የግምገማ እና የክለሳ ስርዓት 36
9. የፖሊሲው ስርጭት 36
10. ፖሊሲው ተፈጻሚ የሚሆንበት ጊዜ 37
11. የቃላት መፍቻ 38

https://t.me/customsclearingagents ..... For More

1. መግቢያ

የአምራች ኢንዱስትሪ ለሀገራዊ ኢኮኖሚ እድገት እና መዋቅራዊ ሽግግርን ለማሳለጥ ወሳኝ ሚና ያለው ሲሆን ባለፉት አመታት ለውጪ ምንዛሪ ግኝት፣ የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት በመሳብ፣ ከውጪ የሚገቡ ምርቶችን በሀገር ውስጥ ምርት በመተካት እና ዘላቂ የስራ ዕድል ፈጠራ አስተዋፅያው እያደገ የመጣና በ2013 በጀት ዓመት ከአጠቃላይ ሀገራዊ ምርት ውስጥ የ 6.8 በመቶ ድርሻ ያስመዘገብ ዘርፍ ነው። ይህንን ዘርፍ ለመምራት የኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂ በ1994 ዓ.ም ተቀርፆ ስራ ላይ መዋሉ ይታወቃል። ይህንኑ እና በሂደት በዳበሩ ሌሎች የፖሊሲ አቅጣጫዎች መሠረት የተተገበሩ ተከታታይ የልማት ዕቅዶች ለአምራች ኢንዱስትሪው ልማት ትኩረት ተሰጥቶት በሀገራዊ ኢኮኖሚ ውስጥ የበኩሉን ድርሻ እንዲጫወት አስችሎታል።

ሆኖም የአምራች ኢንዱስትሪ የማምረት አቅም ማሳደግ እና የምርት ተወዳዳሪነት በሚጠበቀው ሁኔታ ማረጋገጥ ባለመቻሉ ከዘርፉ የሚጠበቀውን ያህል የውጭ ምንዛሪ ግኝት እና የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ ማፋጠን ባለመቻሉም ሀገራችንን ከውጭ በሚገቡ የኢንዱስትሪ ግብዓት ምርቶች እና ፍጆታ ምርቶች ላይ ጥገኛ አድርጓል። ይህም ለሀገራዊ ንግድ ሚዛን ጉድለት የአምራች ኢንዱስትሪ በሚፈለገው ፍጥነት አለማደጉ እንደምክንያት ይጠቀሳል። በአብዛኛው በኢኮኖሚ የአደጉ ሀገራት ልምድም በዋናነት በአምራች አንዱስትሪ ልማት ስኬት እንደሆነ ያሳያል።

ሰለሆነም በሀገራችን የአምራች ኢንዱስትሪው በኢኮኖሚው ውስጥ ሊኖረው የሚገባውን ድርሻ ለማሳደግ እና ያልተፈቱ ጉዳዮች በመመለስ የመልማት አቅምንና መልካም አጋጣሚዎች አሟጠ ለመጠቀም፣ ከዘርፉ ተለዋዋጭ ባህሪያት ጋር የሚመጡ የምርት ስርዓት ለውጥ ለማሰተናገድ እና ከሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ ፕሮግራም ጋር ለማጣጣም በስራ ላይ ያለው ስትራቴጂና የፖሊስ አቅጣጫዎች ተሻሽሎ ይህ ወጥና አካታች የአምራች ኢንዱስትሪ ፖሊሲ በአዲስ መልክ ተዘጋጅቷል።

https://t.me/customsclearingagents ..... For More

2. የፖሊሲው አስፈላጊነት

የአምራች ኢንዱስትሪ ፖሊሲ መንግስታት የየሀገራቸውን የተፈጥሮ፣ የሰው ሀብትና የቴክኖሎጂ አቅም በመጠቀም ዘርፉን ለማልማት እና ለሀገራዊ የኢኮኖሚ ድርሻ ለማሳደግ ያላቸውን አላማ የሚገልፁበት ሰነድ ነው። ይህም በዘርፉ ልማት ሚና ያላቸው ማለትም መንግስት፣ የግሉ ባለሃበት፣ የማህበራትና የሌሎች መንግስታዊ ያልሆኑ ባለድርሻ አካላት የተናጥልና የጋራ ተግባርና ሀላፊነት የሚያመላክት ነው። በተጨማሪ የአምራች ኢንዱስትሪ ከግብርና፣ ማዕድን፣ ኮንስትራክሽን፣ አገልግሎትና ንግድ ዘርፎች ጋር ተቀናጅተው ለጠቅላላዉ ሀገራዊ የኢኮኖሚ ልማት ስኬት የሚኖራቸውን ድርሻ የሚያመለክት ነው። በመሆኑም ፖሊሲው ሀገራት የዘርፉን እድገት ለመምራት፣ ለማፋጠንና ያልተገቡ ድርጊቶችን ለመቆጣጠር አስፈላጊ የሆኑ ፖሊሲዎች፣ ህጎች፣ ስትራቴጂና የትግበራ ስልቶች አቀናጅቶ ለመተግበር ያላቸውን ቁርጠኝነት በግልጽ የሚያሳዉቁበት ሰነድ ነው፡፡

በመሆኑም መንግስት በ1994 ዓ.ም. ተዘጋጅቶ ሲተገበር የቆየው የኢ.ፌ.ድ.ሪ የኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂ ለአልሚ ባለሀብቶች የተመቻቸ ሁኔታ የመፍጠር አስፈላጊነት ፣ የፈፃሚ ተግባርና ሀላፊነት እንዲሁም በመንግስትና በግሉ ዘርፍ፣ በኢንዱስትሪ ባለሀብቱና አርሶ አደሩ፣ በአሰሪና ሰራተኛ መካከል መኖር ስለሚገባዉ ቅንጅት፣ በአጠቃላይ ቅንጅቱ የሚመራባቸው መርሆች፣ አቅጣጫዎችና የአፈጻጸም ስልቶች በማመላከት ከነውስንነቱም ቢሆን ለሀገራችን የኢንዱስትሪ ልማት መነቃቃት አስተዋፅየ አድርጓል፡፡ ይህንን ተከትሎ መንግስት በከፍተኛ ወጪ መሰረተ ልማቶች ማስፋፋት፣ የኢንዱስትሪ ፓርኮችና ሼዶች መገንባት፣ በዘርፉ ለተሰማሩ የሀገር ውስጥ እና የውጭ ባለሀብቶች ፋይናንስና ፋይናንስ ያልሆኑ የተለያዩ ማበረታቻዎችን አቅርቧል። ይሁን እንጂ ስትራቴጂዉ ትግበራ ላይ በቆየባቸው ሁለት አስርት አመታት ውስጥ የታቀዱ ውጤቶች በተለያዩ ምክንያቶች በሚፈለገው ደረጃ ማሳካት አልተቻለም። በሁለቱ የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅዶች አምራች ኢንዱስትሪው ለአጠቃላይ ሀገራዊ ምርት የሚኖረው ድርሻ 12.4 በመቶ ለማድረስ ታቅዶ ከ6.8 በመቶ ማለፍ አልቻለም። በስራ እድል ፈጠራ፣ በውጭ ምንዛሪ ግኝት፣ ገቢ ምርቶችን በመተካት እና የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት በመሳብ የታቀዱ ግቦች አልተሳኩም። ለዚህም የአምራች ኢንዱስትሪዎች ምርትማነትና የማምረት አቅም አጠቃቀም

https://t.me/customsclearingagents ..... For More

እንዲሁም የቴክኖሎጂ አጠቃቀምና ሽግግር ዝቅተኛነት እንደ ዋና ምንክንያት ይጠቀሳል። ለዚህ የአፈፃፅም ክፍተት ከተለዩ ጉድለቶች መካከል አንዱና ዋነኛዉ ዘርፉ ሲመራበት የነበረዉ ስትራቴጂ ግልፅ ወጥና አካታች ወደ ሆነ ፖሊሲ አለማደጉ ወይም የኢንዱስትሪ ፖሊሲ አለመኖሩ ሲሆን ወጥና አካታች የአምራች ኢንዱስትሪ ፖሊሲ በአዲስ መልክ ማዘጋጀት አስፈለጓል።

በሌላ በኩል ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ ፕሮግራም ተቀርጾ ወደ ትግበራ መሸጋገሩ ይህንኑ ተከትሎ ለአምራች ኢንዱስትሪ ልማት ከፍተኛ ሚና ባላቸዉ የኢኮኖሚ ዘርፎች ከተደረጉ የፖሊሲ ማሻሻያዎች ጋር የተጣጣመ የአምራች ኢንዱስትሪ ፖሊሲ በማዘጋጀት የዘርፉን አለም አቀፍ ተወዳዳሪነት፣ ምርትና ምርታማነት ማሻሻል ወደ ንግድና አገልግሎት ዘርፍ ያዘነበለውን የባለሀብቶች የኢንቨስትመንት ፍላጎት ወደ አምራች ዘርፉ ለማሸጋገር የሚያስችል ወቅቱንና የዘርፉን ተለዋዋጭ ባህርያት ያገናዘበና ዉጤትን መሰረት ያደረገ የማበረታቻ ስርዓት በመዘርጋት አምራች ኢንዱስትሪ የታለመውን የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግር እንዲያሳካ በማስፈለጉ ነው።

3. የፖሊሲው ርዕይ፣ ግብ፣ ዓላማዎችና መርሆች

ርዕይ

- ኢትዮጵያ በአፍሪካ ቀዳሚ የአምራች ኢንዱስትሪ ማዕከል ሆና ማየት

ግብ

የፖሊሲው ዋና ግብ የአምራች ኢንዱስትሪ ለሀገራዊ የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግር መረጋገጥ ያለውን ጉልህ ድርሻ ማሳደግ ሲሆን የሚከተሉት ዝርዝር ግቦች ይኖሩታል።

- ፈጣን፣ አካታችና ዘላቂ የአምራች ኢንዱስትሪ ዕድገት ማስመዝገብ፣
- የአምራች ኢንዱስትሪ ለጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ድርሻ ማሳደግ፣
- የአምራች ኢንዱስትሪ የውጪ ምንዛሪ ገቢ መጠንና ድርሻ ማሳደግ፣
- ከውጪ የሚገባ የአምራች ኢንዱስትሪ ምርት በሀገር ውስጥ ምርት የመተካት መጠንና ድርሻ ማሳደግ፣

https://t.me/customsclearingagents ..... For More

- በአምራች ኢንዱስትሪ የሚፈጠር የስራ እድል መጠንና ድርሻ ማሳደግ እና የሰራተኞች ገቢና የኑሮ ደረጃ ማሻሻል ናቸው፣

አላማዎች

የፖሊሲዉ ዋና አላማ የአምራች ኢንዱስትሪውን ምርታማነትና ተወዳዳሪነትን ማሳደግ ሲሆን የሚከተሉት ዝርዝር አላማዎች አሉት።

- ለአምራች ኢንዱስትሪ ምቹ ስነ-ምህዳር መፍጠር፣
- የአምራች ኢንዱስትሪ የሀገር ውስጥ እና የውጪ ኢንቨስመንት መጠን ማሳደግ፣
- የአምራች ኢንዱስትሪውን የሰው ሃይል ምርታማነት ማሳደግ፣
- የአምራች ኢንዱስትሪ ወደ ከፍተኛ ቴክኖሎጂ የምርት ስርዓት ማሻገር፣
- የአምራች ኢንዱስትሪ የማምረት አቅም፣ እሴት ጭመራ እና ጥራት ማሳደግ፣
- የአምራች ኢንዱስትሪውን የአካባቢ እና ማህበራዊ አካታችነትና ዘላቂነት ማሳደግ፣

መርሆዎች

የአምራች ኢንዱስትሪ ፖሊሲዉን ውጤታማ ለማድረግ ፖሊሲው በሚከተሉት መርሆዎች መሰረት የሚመራ ይሆናል።

- **ገበያ መር፡** የአምራች ኢንዱስትሪ ልማት አቅጣጫ ይከተላል፣
- **በግሉ ዘርፍ የሚመራ፡** የግሉ ዘርፍ በአምራች ኢንዱስትሪ ልማት ውስጥ መሪ ተዋናይ ይሆናል። የአምራች ኢንዱስትሪ ልማት የሀገር ውስጥ አምራቾች የሚያሳድግ፣ የሀገር ውስጥና የውጪ ባለሃበትን አቀናጅቶ መጠቀም እና የውጪ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንትን የማስፋፋት አቅጣጫ ይከተላል፣
- **ግልፅ የመንግስት ሚና፡** መንግስት ምቹ የአምራች ኢንዱስትሪ ስነ-ምህዳር መፍጠር በተለይም የተቀናጀና የተናበበ የመንግስት አገልግሎት ማቀረብ እንዲሁም ኢንቨስትመንት በግሉ ዘርፉ ሊተገበሩ የማይችሉትን ስትራቴጂክ ምርቶች አዋጪነቱን በጠበቀ መንገድ የገበያ ጉድለቱን ይሞላል፣ ከግሉ ዘርፍ ጋር በመቀናጀት ለአምራች ኢንዱስትሪ ልማት በትኩረት ይሰራል፣

https://t.me/customsclearingagents ..... For More

- **የኢንዱስትሪ ክላስተር፡** የአምራች ኢንዱስትሪ ልማት የተቀናጀ ግብዓትና ምርትን መሰረት ያደረገ ኢንዱስትሪ ክላስተር ይከተላል፣ ይህም የአካባቢ የተፈጥሮ ፀጋን ያገናዘበ፣ የከተማና ገጠር ትስስርን የሚያጠናክር እና ከአካባቢ ልማት ዕቅድ ጋር በተጣጣመ የኢንዱስትሪ ማፕ እንዲመራ ይደረጋል፣
- **ለወጪና ተኪ ምርት ተመጣጣኝ ትኩረት የሰጠ፡** የአምራች ኢንዱስትሪ ምርቶች ለውጪ ገበያ ማቅረብና ከውጪ የሚገቡ ምርቶች በሀገር ውስጥ ምርት መተካት ሚዛኑን በጠበቀ መልኩ ይመራል፣
- **አካታችና ዘላቂ አምራች ኢንዱስትሪ ልማት፡** የፖሊሲው ትግበራ አካታችና ዘላቂ የአምራች ኢንዱስትሪ ልማትን ያረጋግጣል፣
- **የተጣጣመ የህግ ማዕቀፍ ፡** ሀገራችን አባል የሆነችባቸውን የአካባቢያዊ፣ አህጉራዊ እና ዓለም አቀፋዊ ስምምነቶችን በተጣጣመ ሁኔታ ይፈፅማል፣

4. የፖሊሲው ወሰን

ይህ ፖሊሲ የጥቃቅን፣ የአነስተኛ፣ የመካከለኛና የከፍተኛ አምራች ኢንዱስትሪዎችን ይመለከታል።

5. የፖሊሲ ዋና ዋና ጉዳዮች

የአምራች ኢንዱስትሪ ፖሊሲ ርዕይ፣ ግብና አላማ ለማሳካት የመሰረታዊ የፖሊሲ አቅጣጫ ለውጦች እና የነባሩን ፖሊሲ አቅጣጫዎች ማስፋትና ማጠናከርን አካቷል። እነዚህን የአቅጣጫ ለውጦች በውጤታማነት ለመተግበር በአምስት ዋና ዋና እንዲሁም በዘርፉ ብዙ ጉዳዮች ላይ ማሻሻያ ተደርጓል። ይህም ለአምራች ኢንዱስትሪ የተረጋጋ ማክሮ ኢኮኖሚ እና ምቹ የቢዝነስ ሥነ-ምህዳር፣ የፋይናንስ አቅርቦት፣ ክህሎትና ስራ፣ ሳይንስና ኢኖቬሽን፣ የምርት ልማትና ተወዳዳሪነት እና አካታችነትና ዘላቂነት ዘርፉ ብዙ ጉዳዮች ዋና ዋና የፖሊሲ ጉዳዮች ሆነው ቀርበዋል።

https://t.me/customsclearingagents ..... For More

5.1. የማክሮ ኢኮኖሚና የቢዝነስ ሥነ-ምህዳር

ሀገራዊ የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግሩን እውን ለማድረግ የአምራች ኢንዱስትሪው የሚጠበቅበትን ሚና እንዲወጣ ለዘርፉ የተመቻቸ የማክሮ ኢኮኖሚ ሁኔታ እና አስቻይ የቢዝነስ ሥነ-ምህዳር መፍጠር አስፈላጊ ነው።

5.1.1 ለአምራች ኢንዱስትሪ የተረጋጋ የማክሮ ኢኮኖሚ ሁኔታ የመፍጠር አላማ

የተረጋጋ የማክሮ ኢኮኖሚ ሁኔታ ለአምራች ኢንዱስትሪ ልማት እጅግ ተፈላጊ ከሆኑ መሰረታዊ ሁኔታዎች አንዱ ነው። መንግስት የተረጋጋ ማክሮ ኢኮኖሚ ለመፍጠር የዋጋ ግሽበትን፣ የወለድ ምጣኔና የውጭ ምንዛሬ ተመንን በተመለከተ የተለያዩ የህግ ማዕቀፎችን አውጥቶ ሲተገብር ቆይቷል። በቅርቡም በሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ ፕሮግራም የተተገበሩት የማክሮ ኢኮኖሚና መዋቅራዊ ሪፎርሞች የአምራች ኢንዱስትሪውን ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግና አለም አቀፍ ተወዳዳሪነትን ለማረጋገጥ ተጨማሪ አስቻይ ሁኔታዎች ፈጥሯል።

የአምራች ኢንዱስትሪ በአብዛኛው ከፍተኛ መዋለንዋይ ማፍሰስና ውጤቱም ረዥም ጊዜ የሚጠይቅ በመሆኑ የተረጋጋና ተገማች የማክሮ ኢኮኖሚ መስተጋብር ይፈልጋል። ይህም ዝቅተኛ የዋጋ ግሽበት፣ ተገማችና የተረጋጋ የውጪ ምንዛሪ ፖሊሲ እና ሚዛናዊ የፋይናንስና የሀብት ፍሰት የአምራች ኢንዱስትሪውን በሚደግፍ ሁኔታ መፈጠር አስፈላጊ ነው።

የፖሊሲው አቅጣጫ

- መንግስት የአምራች ኢንዱስትሪ ልዩ ባህሪ ባገናዘበ መልኩ የተረጋጋ የማክሮ ኢኮኖሚ (የውጪ ምንዛሪ ፖሊስን ጨምሮ) እንዲፈጠር ያደርጋል።

የፖሊሲው ማስፈፀሚያ ስልቶች

- የአምራች ኢንዱስትሪውን የሚደግፍ የተረጋጋና ተገማች ማክሮ ኢኮኖሚ አሰራር ስርዓት ይዘረጋል፣

https://t.me/customsclearingagents ..... For More

5.1.2 ለአምራች ኢንዱስትሪ ምቹ የቢዝነስና ኢንቨስትመንት ሥነ-ምህዳር የመፍጠር አላማ

ምቹ የቢዝነስ ከባቢ መፍጠር በአምራች ኢንዱስትሪው ቀጣይነት ያለው ኢንቨስትመንት እንዲኖር እንዲሁም የምርት ተወዳዳሪነትን ለማሳደግ የሚያስችልና የሚያበረታታ ዝቅተኛው መስፈርት ነው። መንግስት የአምራች ኢንዱስትሪ ልማት በግል ዘርፉ የሚመራ በተለይም በውጪ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንትን መሳብ ላይ ያተኮረ እና ከሀገር ውስጥ ባለሃብት ጋር መዋለንዋይ ማፍሰስን የሚያበረታታ አሰራር ዘርግቷል። የኢንዱስትሪ ፓርኮች አስተዳደር አዋጅ የፓርኮች ልማት በመንግስትና በግል ዘርፉ እንዲስፋፋ አመቺ ሁኔታዎችን ፈጥሯል። በ2013 ዓ.ም. የተሻሻሉት የኢንቨስትመት እና የንግድ ህጎች ቀልጣፋ የቢዝነስ ስርዓት ደረጃን ለማሻሻል የተወሰዱ እርምጃዎች ለአምራች ኢንዱስትሪው ተጨማሪ አስቻይ ሁኔታዎችን ፈጥረዋል። የአምራች ኢንዱስትሪ ልዩ ባህሪያትን ባገናዘበ ሁኔታ የሀገር ውስጥ አምራች ድጋፍና ማበረታቻ፣ የቴክኖሎጂ ሽግግር፣ የውጭ ኢንቨስተሮች ጥራት ክትትል እና የግብዓት ትስስር በተጠናከረ የአሰራር ስርዓት መምራት ያስፈልጋል።

የአምራች ኢንዱስትሪ ቢዝነስና ኢንቨስትመንት ከባቢ (የፓርኮችና ሌሎች የኢኮኖሚ ዞን መዘርጋትን ጨምሮ) ቀልጣፋና ግልፅ እንዲሆን በማድረግ የግል ኢንቨስትመንት ማስፋፋት ያስፈልጋል። ይህም የውጪ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት፣ የሀገር ውስጥ አምራች እና የውጪና የሀገር ውስጥ አምራች ሽርክናን ባገናዘበ ሁኔታ የአምራች ኢንዱስትሪ ኢንቨስትመንት መሳብ አስፈላጊ ነው። እንዲሁም የአምራች ኢንዱስትሪ የታክስ ምዘገባ እና የደረሰኝ ግብይት ቁጥጥር ስርዓት የሚያስተሳስር የአሰራር ስርዓት ማጠናከር አስፈላጊ ነው። የአምራች ኢንዱስትሪ የማምረቻ ቦታ አቅርቦት አሰራር በተለይም የመንግስት የኢንዱስትሪ ፓርኮች ለውጪ ንግድ ኢንቨስትመት ትኩረት ከማድረጉ በተጨማሪ በተኪ ምርት ላይ የተሳተፉ የሀገር ውስጥ አምራች ማሳተፍ አስፈላጊ ነው። በዘርፉ የመንግስት ኢንቨስትመንት በግሉ ዘርፍ ሊተገበሩ የማይችሉትን ስትራቴጂክ ምርቶች አዋጪነቱን በጠበቀ መንገድ የገበያ ጉድለቱን መሙላት ላይ ብቻ በማተኮር ለግሉ ዘርፍ የመወዳደሪያ ምህዳሩን ማስፋት አስፈላጊ ነው።

https://t.me/customsclearingagents ..... For More

የፖሊሲው አቅጣጫ

- የአምራች ኢንዱስትሪ ኢንቨስትመንት ማስፋፊያ ስርዓቱ የዘርፉን ልዩ ባህሪያት ባገናዘበ መልኩ ይዘረጋል። ይህም የሀገር ውስጥ አምራች፣ የውጪ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት፣ የውጪና የሀገር ውስጥ አምራች ሽርክና እና የኮንትራት ማኑፋክቸሪንግ በሚያበረታታ መልኩ የአሰራር ስርዓቶች ይጠናከራሉ፣
- የሀገር ውስጥ አምራች ኢንዱስትሪ የምርታማነት ማዕቀፍን የሚያሳድግ አሰራር ስርዓት እንዲመራ ይደረጋል፣
- የአምራች ኢንዱስትሪ የታክስ ምዝገባ እና የደረሰኝ ግብይት ቁጥጥር ስርዓት የሚያስተሳስር የአሰራር ስርዓት እና ቢዝነስ ለመስራት የሚያስችል ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር የዘርፉን ልዩ ባህሪያት ባገናዘበ መልኩ እንዲሻሻል ይደረጋል፣
- የኢንዱስትሪ ፓርክ አሰራር በግሉ ዘርፍ እንዲሁም በግሉና በመንግስት የጋራ ቅንጅት እንዲለማና እንዲመራ ይደረጋል፣ የቴክኖሎጂ ሽግግር እና የግብዓት ምርት ትስስር እንዲጠናከር ድጋፍና ማበረታቻ ይደረጋል፣
- የመንግስት ኢንቨስትመንት በግል ዘርፉ ሊሰሩ የማይችሉትን ዘርፎች በቅድመ አዋጭነትና የውጤታማነት መከታተያ የተጠናከረ ስርዓት በመዘርጋት መንግስት ስትራቴጂክ በሆኑ ምርቶች ላይ ብቻውን ወይም ከግል ባለሃብቱ ጋር በቅንጅት የገበያ ጉድለቱን ይሞላል።

የማስፈፀሚያ ስልቶች

- የአምራች ኢንዱስትሪ ኢንቨስትመንት አሰራር ስርዓት ይዘረጋል፣ የተቀናጀ መዋቅራዊ አደረጃጀት ይዘረጋል፣
- የአምራች ኢንዱስትሪ ቢዝነስ ለመስራት የሚያስችል ምቹ ሁኔታ አሰራር የዘርፉን ልዩ ባህሪያት ባገናዘበ መልኩ ይሻሻላል፣
- የሀገር ውስጥ አምራች ኢንዱስትሪ የምርታማነት የሚያሳድግ ስርዓትና የልዩ ድጋፍ አሰራር ይዘረጋል፣
- የጥቃቅን፣ አነስተኛና መካከለኛ አምራች ኢንተርፕራይዝ ስትራቴጂ የአምራች ኢንዱስትሪን መሰረት በሚያስፋፋ መልኩ ይሻሻላል፣
- የኢንዱስትሪ የፓርኮችና ልዩ የኢኮኖሚ ዞን ስርዓት ይሻሻላል፣

https://t.me/customsclearingagents ..... For More

- የመንግስት የአምራች ኢንዱስትሪ ኢንቨስትመንት ስርዓት ይሻሻላል፣

5.1.3 ለአምራች ኢንዱስትሪ የመሬትና የማምረቻ ቦታ አቅርቦት የማሳደግ አላማ

የአምራች ኢንዱስትሪውን እድገት ለማሳካት መሬት ስትራቴጂክ የመሰረተ ልማት ሲሆን በሚፈለገው መጠንና ፍጥነት ማቅረብ የተመቻቸ የቢዝነስ ምህዳር ለመፍጠር ወሳኝ ሚና አለው። መንግስት በኢንቨስትመንት ለሚሰማሩ አምራች ኢንዱስትሪዎች የመሬት እና የማምረቻ ቦታ አቅርቦት አሰራሮችን ተግብሯል። መሬት ለአምራች ኢንዱስትሪ በሚፈለገው መጠንና ፍጥነት ማቅረብ መሬትን የበለጠ ውጤታማ በሆኑ መልኩ ለታለመለት አላማ ለማዋልና ዘርፉ ለሀገራዊ ለኢኮኖሚ እድገት የሚጠበቅበት ድርሻ ለማሳደግ ወሳኝ ሚና አለው።

ለአዲስና ነባር የአምራች ኢንዱስትሪዎች መሬትና የማምረቻ ቦታ አቅርቦት በኢንዱስትሪ ማፕ ላይ ተመርኩዞ መሬት የሚከለልበትና በኢንቨስትመንት አይነቶች ተለይተው በምን ያህል ዋጋ እና መጠን መሬትን ማቅረብ የሚያስችል አሰራር መዘርጋት ይገባል። የመሬት አቅርቦት ስርዓት የአካባቢውን ማህበረሰብ ለዘላቂ ልማትና ተጠቃሚነት አካታችነትን ያገናዘበ እንዲሁም የመሬት ማካካሻ ስርዓት የግልፅነትና ወጥነት የተከተለ የመሬትና የማምረቻ ቦታ አቅርቦት ስርዓት መዘርጋት አጭር፣ ግልፅና እና ከሙስና የፀዳ እንዲሆን ያደርገዋል። ለጥቃቅንና አነስተኛ አምራቾች የማምረቻ ሼዶች አቅርቦት ስርዓት የእነዚህን ሽግግር በሚያረጋግጥ መልኩ መምራት ያስፈልጋል።

የፖሊሲው አቅጣጫ፡

- የአምራች አንዱስትሪዎች የመሬትና የማምረቻ ቦታ አቅርቦት የኢንዱስትሪ ማፕን የተመረኮዘ እንዲሆን ይደረጋል፣ ይህም የአካባቢ የመልማት ፀጋ ያገናዘበ የአካባቢ ልማት ዕቅድ ጋር እንዲጣጣም እና ከመሬት/የማምረቻ ቦታ፣ የውሃ፣ የኤሌክቲሪክ ሃይል አቅርቦት፣ የመኖሪያ ቤት ልማት እና ማህበራዊ አገለግሎት አቅርቦት ጋር በተቀናጀ ሁኔታ እንዲመራ ይደረጋል፣
- የአምራች አንዱስትሪዎች የመሬትና የማምረቻ ቦታ አቅርቦት በፌደራል፣ በክልልና በከተማ አስተዳደር ተዋረድ መዋቅር ተጠያቂነት ያለበት፣ ባለሃብቱ የተሰጠውን የመስሪያ ቦታ ለታለመለት ዓላማ ማዋሉን በሚያረጋግጥ ሂደት፣

https://t.me/customsclearingagents ..... For More

የአካባቢውን ማህበረሰብ ለዘላቂ ልማትና ተጠቃሚነት አካታችነትን ያገናዘበ እና አፋጣኝ ምላሽ የሚሰጥና ግልጽ አሠራር እንዲዘረጋ ይደረጋል።

የፖሊሲው ማስፈፀሚያ ስልቶች

- የአምራች ኢንዱስትሪ ማፕ ይዘጋጃል፣
- የአምራች ኢንዱስትሪ የመስሪያ ቦታ አቅርቦት ስርዓት ይዘጋጃል፣
- የአምራች ኢንዱስትሪ የመሬት አቅርቦት ስርዓት ይዘጋጃል፣

5.1.4 ለአምራች ኢንዱስትሪ የኤሌትሪክ ሃይል አቅርቦት የማሳደግ አላማ

ለአምራች ኢንዱስትሪ አስተማማኝ የሃይል አቅርቦት ማረጋገጥ ለኢንዱስትሪው እድገት የማይተካ ሚና አለው። መንግስት የኤሌትሪክ ሃይል ለአምራች ኢንዱስትሪ ለማቅረብ የተለያዩ የታዳሽ ሃይል ምንጮችን በመጠቀም ሃይል ማመንጨትና ማሰራጨት በስፋት ተከናውኗል። የአምራች ኢንዱስትሪው የኤሌክትሪክ ሃይል አቅርቦት በቅድሚያ የሚያገኝበት አሰራርና ተቋማዊ አደረጃጀት እንዲሁም የራሳቸውን ማከፋፈያ ጣቢያና መስመር በመገንባትና በማስተዳደር ከብሔራዊ ግሪድ ሃይል የሚወስዱበት አሰራር ተዘርግቷል።

የአምራች ኢንዱስትሪዎች አስተማማኝ የሃይል አቅርቦትን የሚመራበት በአምራቹና በሃይል አቅራቢው መካከል የተቀናጀ ስርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ነው። ይህም የአምራች ኢንዱስትሪው ለአዳዲስና ማስፋፊያ ኢንቨስትመንት የሚያስፈለገው ሃይል ለመዘርጋት የሚያስችሉ መሰረተ ልማት ለመገንባት የማበረታቻና የማስፈፀሚያ አሰራር ይጨምራል። በቂና ያልተቆራረጠ የኤልክትሪክ ሃይል አቅርቦት ማረጋገጥ በዝቅተኛ የአቅም አጠቃቀም እና ከፍተኛ የማሽን ብልሽት ብሎም በዝቅተኛ ምርታማነት የሚገለፀውን የሀገራችን የአምራች ኢንዱስትሪ ለማሳደግ ይረዳል።

የፖሊሲው አቅጣጫ

- የአምራች አንዱስትሪዎች ልዩ ባህሪያትን ያገናዘበ (የኤሌክትሪክ ሃይል ፍላጎት መሰረት ያደረገ፣ በቂና ያልተቆራረጠ) እና የኢንዱስትሪ ክላስተርን የተከተለ ሃይል አቅርቦት እንዲኖር ይደረጋል፣

https://t.me/customsclearingagents ..... For More

- የአምራች አንዱስትሪዎች የሃይል አቅርቦት በፌደራልና በክልል ተዋረድ መዋቅር ተጠያቂነት ያለበት፣ አፋጣኝ ምላሽ የሚሰጥና ግልጽ አሠራር የሚከተል እንዲሆን ይደረጋል፣
- የአምራች ኢንዱስትሪ አማራጭ ሀይል የሚያመነጭበትና የሚጠቀምበት ማበረታቻና ድጋፍ ይደረጋል፣ የፋይናንስ አቅርቦት ይመቻቻል።

የፖሊሲው ማስፈፀሚያ ስልቶች

- የአምራች ኢንዱስትሪ የተቀናጀ የኤሌክትሪክ ሃይል አቅርቦት ስርዓት ይዘጋጃል፣
- በአምራች ኢንዱስትሪውና በሃይል አቅራቢው መካከል የሃይል ግዥና ሽያጭ የውል ስምምነት (በሃይል መቆራረጥ ምንክያት የሚመጡ ጉዳቶችን ተጠያቂ የሚያደርግ እና ምላሽ የሚሰጥበት አሰራርን ጨምሮ) ስርዓት ይዘረጋል፣

5.1.5 ለአምራች ኢንዱስትሪ የትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ አቅርቦት የማሻሻል አላማ

የአምራች ኢንዱስትሪ ልማት ስኬታማነት ለማረጋገጥ ከሚያስፈልጉ አስቻይ ሥነ ምህዳር አንዱ አስተማማኝ የትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ አገልግሎት በተመጣጣኝ ዋጋና ቅልጥፍና ከዘርፉ ልዩ ባህሪያት ጋር በተስማማ ሁኔታ ማቅረብ ሲቻል ነው። ለዚህም መንግስት የመንገድ መረብ ማስፋት በተለይም ደረጃውን የጠበቀ የመንገድ ዝርጋታና ጥገና አካሂዷል። በተመሳሳይም የአዲስ አበባ ጅቡቲ የባቡር መስመርን ማሻሻል እና ሌሎች አማራጭ ወደቦች ጋር የሚያስተሳስሩ የባቡር መስመሮች ዝርጋታ፣ የደረቅ ወደብ ግንባታ እና የአየር ትራንስፖርት አገልግሎት ማስፋፋት ትኩረት ተሰጥቶ ተከናውነዋል። በ2014 ዓ.ም. የብሔራዊ ሎጅስቲክስ ፖሊስና ስትራቴጂ ተዘጋጅቶ ወደ ስራ ተግብቷል። ይህም የአምራች ኢንዱስትሪውን ተጠቃሚ አድርጎታል።

የሀገራችን የትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ አገልግሎት ዝርጋታ የኢንዱስትሪ ልማቱን የተከተለ ማድረግ ብሎም የአገልግሎት አሰጣጥ ደረጃ፣ ብቃት እና ተጠያቂነት እንዲሁም የዋጋ ተወዳዳሪነትን ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው። በተጨማሪም የሎጅስቲክስ አገልግሎት አቅርቦት በማስፋት ዘመናዊ የምርት ማጓጓዣ፣ ማሸግ፣ የመጋዘን አስተዳደር፣ የትራንስፖርት አስተዳደር አገልግሎት እና የኢንቬንቶሪ አስተዳደርን ማቅረብ የሚያስችሉ አሠራሮችን መዘርጋት ይፈልጋል። ይህም የአምራች ኢንዱስትሪ

https://t.me/customsclearingagents ..... For More

የወጪና ገቢ ንግድ እንዲሁም የሀገር ውስጥ የግብዓት ምርት ትስስር ለማሳለጥ ትልቅ ድርሻ ይኖረዋል።

የፖሊሲው አቅጣጫ

- የአምራች አንዱስትሪዎች የትራንስፖርት ዝርጋታና አገልግሎት አቅርቦት የወጪና ገቢ ንግድ እንዲሁም የሀገር ውስጥ የግብዓት ምርት ትስስር ለማሳለጥ የሚያግዝ ዘመናዊ የትራንስፖርት አገልግሎት እንዲስፋፋ ይደረጋል።
- የአምራች አንዱስትሪዎች ሎጂስቲክስ ዝርጋታ እና አገልግሎት አቅርቦት የኢንዱስትሪ ልማት የተከተለ እና የሚደግፍ እንዲሆን ይደረጋል።
- የአምራች አንዱስትሪዎች የወጪና ገቢ ንግድ እንዲሁም የሀገር ውስጥ የግብዓት ምርት ትስስር ለማሳለጥ የሚያግዝ ዘመናዊና ተጨማሪ ሎጂስቲክ አገልግሎት እንዲስፋፋ ይደረጋል፣ ይህም በግሉ ዘርፍ እና በመንግስትና የግሉ አጋርነት እንዲዘረጋ ይደረጋል።

የፖሊሰው ማስፈፀሚያ ስልቶች

- የአምራች አንዱስትሪዎች የትራንስፖርት ዝርጋታና አገልግሎት አቅርቦት የዘርፉ ልዩ ባህሪያ ባገናዘበ መልኩ አሰራርና ስርዓት ይዘረጋል፣
- የአምራች ኢንዱስትሪ ሎጂስቲክስ ዝርጋታና አገልግሎት አቅርቦት የዘርፉ ልዩ ባህሪያ ባገናዘበ መልኩ አሰራርና ስርዓት ይዘረጋል፣

5.1.5 ለአምራች ኢንዱስትሪ የጉምሩክ አገልግሎት አቅርቦት የማሻሻል አላማ

የአምራች ኢንዱስትሪ የገቢና ወጪ ንግድ ለማሳለጥ የጉምሩክ አገልግሎት አንዱ አስቻይ ሁኔታ ነው። መንግስት አገልግሎቱን በተገቢው መንገድ ለማቅረብ እና አለም አቀፍ የንግድ እንቅስቃሴ ከደረሰበት የዕድገት ደረጃ ጋር ለማጣጣም የተለያዩ ማሻሻያዎች ተተግብረዋል። የአምራች ኢንዱስትሪ ልዩ ባህሪያት ያገናዘበና ቀልጣፋ የጉምሩክ አሰራር በተለይም የማምረቻ ግብዓት ትመና ፣ የግብዓት ምርት ጥምርታ፣ የግዢ ደረሰኝ ትክክለኛነት የሚያረጋግጥ የአሰራርና ቁጥጥር ስርዓት፣ የድህረ እቃ አወጣጥ አዲት ስርዓት ማዘመን ያስፈልጋል። በተጨማሪም የማምረቻ ግብዓት ትመና ክህሎት፣ ግልፅና ወቅታዊ የጉምሩክ ዋጋ መረጃ፣ የጉምሩክ ባለሙያ እና የጉምሩክ አስተላላፊ ተጠያቂነት፣ የቀረጥና ታክስ ድህረ ክፍያ፣ የተገልጋዮች የአገለግሎት

https://t.me/customsclearingagents ..... For More

መስጫ ጊዜ ስታንዳርድ፣ የተመረጡ የልዩ መብት ተጠቃሚዎች አገልግሎት፣ የጉምሩክ መጋዘን አስተዳደር እና ኮንትሮባንድ ቁጥጥር ማሻሻል አስፈላጊ ናቸው።

የፖሊሲው አቅጣጫ

- የአምራች ኢንዱስትሪ የጉምሩክ አገልግሎት የዘርፉን ልዩ ባህሪያት ባገናዘበ መልኩ ይሻሻላል።

የፖሊሲው ማስፈፀሚያ ስልቶች

- የአምራች ኢንዱስትሪ የጉምሩክ አገልግሎት አሰራር ስርዓት ይሻሻላል፣

5.1.6 የአምራች ኢንዱስትሪ የማበረታቻ ስርዓት ውጤት ተኮር የማድረግ አላማ

መንግስት የአምራች ኢንዱስትሪ ልማትን ለማፋጠን እና ለባለሃብቱ የተመቻቸ ሁኔታን ለመፍጠር የተለያዩ የማበረታቻ ስርዓትን ዘርግቷል። የማበረታቻ ስርዓቶቹ የአምራች ኢንዱስትሪውን ልዩ ባህሪያት ያገናዘቡ እና የማበረታቻው ውጤታማነት የሚለካበት ስርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ነው። ይህም የመንግስትን ውስን ሃብት በአግባቡ ለማስተዳደር ብሎም የላቀ አፈፃፀም የሚያስመዘግቡ አምራች ኢንዱስትሪዎችን ለይቶ በማበረታታት ለዘርፉ እድገት ቀጥተኛ አስተዋፆ እንዲያበረክት ያስችለዋል።

የፖሊሲው አቅጣጫ

- የአምራች ኢንዱስትሪ የማበረታቻ ስርዓት የሀገር ሀብትን በሚቆጥብና ለዘርፉ እድገትና ውጤታማነት የሚጠበቅበትን አስተዋፅዖ እንዲያበረክት ሆኖ በውጤት ላይ የተመረኮዘ የማበረታቻ ስርዓት ይተገበራል።

የፖሊሲው ማስፈፀሚያ ስልቶች

- የአምራች ኢንዱስትሪ በአፈፃፀም ላይ የተመሠረተ የውጤት ተኮር የማበረታቻ ማዕቀፍ ስርዓት ይዘረጋል፣ ጠንካራ ክትትልና ቁጥጥር ይዘጋጃል፣ የተቀናጀ ተቋማዊ አደረጃጀት ይዘረጋል፣

https://t.me/customsclearingagents ..... For More

5.1.7 ለአምራች ኢንዱስትሪ የተመቸ ግልፀኝነትና ተጠያቂነት የሰፈነበት የመንግስት አገልግሎት የማቅረብ አላማ

የመንግስት አገልግሎት በተዋረድ መዋቅሮች ግልጽ፣ ውጤታማ፣ ፈጣንና፣ በሕግና በአስተዳደራዊ ሂደት ተጠያቂነት ያለበት አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግ የአምራች ኢንዱስትሪውን ለማስፋፋት አንዱና ዋነኛው መደላድል ነው። መንግስት ጠንካራ የአመራር ሚና የሚጫወትበት አቅጣጫ እና ግልፅ፣ ተጠያቂና ቀልጣፋ አገለግሎት ማቅረብ፣ ልማትን የሚደግፍ የግብር እና መረጃ ስርዓት መዘርጋት እንዲሁም ቀልጣፋ የፍትህ አስተዳደር ስርዓት መፍጠር ለኢንዱስትሪ ቀጣይነት ያለው ሚና ወሳኝ በመሆኑ የሲቪል ሰርቨስ ማሻሻያ ጨምሮ የተለያዩ ስርዓቶች ተተግብረዋል። የአምራች ኢንዱስትሪ ልዩ ባህሪያትን ያገናዘበ የመንግስት አገልግሎት ሊያቀርብ የሚችል የመንግስት ሰራተኛ ተጨማሪ የማትጊያና ተጠያቂነት (ውጤታማነት መከታተያ) ስርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ነው። የመንግስት ተቋማት በተዋረድና በጎንዮሽ ተናበውና ተቀናጅተው የሚሰሩበት የትብብርና ተጠያቂነት አሰራር መዘርጋትና የተልዕኮ ግጭት ማስቀረት ቀልጣፋና ተጠያቂ የሆነ የመንግስት አገልግሎት እና ለባለሀብቱ በቂ ድጋፍና ክትትል ለማካሄድ ወሳኝ ነው። የአምራች ኢንዱስትሪ ምርትማነትና ተወዳዳሪነትን የሚመራ የመንግስት ከፍተኛ ውሳኔ ሰጪ አካል መምራትና ንቅናቄ መፍጠር ይጠይቃል።

የፖሊሲው አቅጣጫ

- የአምራች ኢንዱስትሪን ልዩ ባህሪያት ባገናዘበ መልኩ የሰው ሃይል የሚመራበት የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ይደረጋል፣
- የአምራች ኢንዱስትሪን የሚደግፉ በተዋረድ የሚገኙ የመንግስት ተቋማት ተጠያቂነት የሰፈነበት ውጤታማ ግንኙነት እንዲኖራቸው ይደረጋል፣
- የአምራች ኢንዱስትሪ የመንግስት አገልግሎት አቅርቦት ስርዓት እንዲጠናከር ይደረጋል፣
- የአምራች ኢንዱስትሪ በጠንካራ ቁጥጥር ስርዓት እና በተቀናጀ ተቋማዊ አደረጃጀት እንዲመራ ይደረጋል፣

https://t.me/customsclearingagents ..... For More

- የአምራች ኢንዱስትሪ በጠንካራ የመንግስት ከፍተኛ ውሳኔ ሰጪ አካል እንዲመራ እና የምርታማነትና ተቀዋዳሪነት ቀጣይነት ያለው ንቅናቄ እንዲፈጠር ይደረጋል።

የፖሊስው ማስፈፀሚያ ስልቶች

- የአምራች ኢንዱስትሪውን የሚደግፉ የመንግስት ተቋማት በተዋረድና በጎንዮሽ ተናበውና ተቀናጅተው የሚሰሩበት የትብብርና ተጠያቂነት አሰራር ይዘረጋል፣
- የአምራች ኢንዱስትሪ ልዩ ባህሪያትን ያገናዘበ የመንግስት አገልግሎት ሊያቀርብ የሚችል የሲቪል ሰርቪስ የማትጊያና ተጠያቂነት ስርዓት ይሻሻላል፣
- የአምራች ኢንዱስትሪ የመንግስት አገልግሎት አቅርቦት ስርዓት የሆኑ (የተሳለጠና የተሰናሰነ የአንድ መስኮት አገልግሎትን ማጠናከር፣ የመንግስት አገልግሎት ጥራት ስራ አመራር፣ የዲጂታል አገልግሎት፣ የተገልጋዮች የአገልግሎት መስጫ ጊዜ ስታንዳርድ፣ የተመረጡ የልዩ መብት ተጠቃሚዎች አገልግሎት ጨምሮ) ይሻሻላል፣
- የአምራች ኢንዱስትሪ በጠንካራ ቁጥጥር ስርዓት እና የተቀናጀ ተቋማዊ አደረጃጀት ይሻሻላል፣
- የአምራች ኢንዱስትሪ የመንግስት ከፍተኛ ውሳኔ ሰጪ አካል አመራር ስርዓትና መዋቅራዊ አደረጃጀት ይዘረጋል፣

5.2. ፋይናንስ

ለአምራች ኢንዱስትሪ በቂና ውጤታማ ፋይናንስ ለማቅረብ የተጠናከረ የብድር አቅርቦት፣ የውጪ ምንዛሪ ፣ የመድን ሽፋን እና ባንክ ያልሆኑ ሌሎች የፋይናንስ ምንጮችን መጠቀም ያስፈልጋል።

5.2.1 ለአምራች ኢንዱስትሪ የብድር አቅርቦት የማሳደግ አላማ

ለአምራች ኢንዱስትሪ የረዥም ጊዜ የፕሮጀክት እና የስራ ማስኬጃ ብድር በበቂ መጠንና ዋጋ ቀልጣፋና ግልፅ የሆነ አሰራር መዘርጋት ያስፈለጋል። የፖሊሲ ባንክ የሆነው ልማት ባንክ ለአምራች ኢንዱስትሪ አዋጭ ለሆኑ ፕሮጀክቶች የረጅም ጊዜ ብድር፣ የመሳሪያ ሊዝን አቅርቦት፣ የግብዓት ብድር፣ የወጪ ንግድ ብድር እና

https://t.me/customsclearingagents ..... For More

ለደንበኞች የስራ ማስኬጃ ብድር እንዲሁም ለማይክሮ ፋይናንስ ተቋማት የጥቅል ብድር የሚያቀርብበትና ከንግድ ባንኮች ጋር በቅንጅት የሚሰራበት ሁኔታዎች ተከናውነዋል። የንግድ ባንኮች ለአምራች ኢንዱስትሪው በዋናነት የስራ ማስኬጃ ብድርና በተወሰነ መልኩ የረጅም ጊዜ ብድር አቅርቧል። የማይክሮ ፋይናንስ ተቋማት) ለአምራች ኢንዱስትሪው በተለይም ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የመሳሪያ ሊዝ፣ መነሻ ካፒታልና የብድር አቅርቦት ሲያቀርቡ ቆይተዋል።

የአምራች ኢንዱስትሪ በአብዛኛው ከፍተኛ መዋለንዋይ ማፍሰስና ውጤቱም ረዥም ጊዜ የሚጠይቅ በመሆኑ ይህንን ልዩ ባህሪያ የሚያስተናግድ የፋይናስን አቅርቦት ይፈልጋል። ለዘርፉ የረጅም ጊዜ የፕሮጀክት እና የስራ ማስኬጃ ብድር የሚያቀርብ የፖሊሲ ባንክ አስፈላጊ ሲሆን የብድር አቅርቦቱም ግልፅ፣ አሳድርና የተሳለጠ፣ ወጪ ቆጣቢ እና ውጤታማ የድህረ ብድር ድጋፍና ክትትል የሚያከናውን መሆን ይኖርበታል። በሌላ መልኩ የብድር ተቋማት የአምራች ኢንዱስትሪው የሚፈልገውን የረጅም ጊዜ የፕሮጀክት ብድር እና የስራ ማስኬጃ ብድር ለማሳደግ ድርጋፍና ማበረታቻ ያስፈልጋቸዋል። የብድር መያዣ ዋስትና ቋሚ ያልሆኑ ንብረቶችን እና ሌሎች አሰራሮችን እንዲያካትት ማድረግ ያስፈልጋል።

የፖሊሲው አቅጣጫ

- የአምራች ኢንዱስትሪዎችን የብድር አቅርቦት ለማሻሻል የፖሊሲ ባንክና ንግድ ባንኮች ዘርፉ ካለው ሁለንተናዊ አስተዋፅኦ አንፃር የሚያበረታታ የብድር ድርሻ እንዲያድግ እና የብድር አይነቶች እንዲሰፉ ይደረጋል።
- ለአምራች ኢንዱስትሪዎ ባሕሪያትን ያገናዛበ የብድር ዋስትና አይነቶች እንዲያሰፉ ይደረጋል።
- የፖሊሲ ተግባርን የሚወጣ የአምራች ኢንዱስትሪ ባንክ ይቋቋማል።

የማስፈፀሚያ ስልቶች

- ባንኮች (ወለደ አልባ ባንኮች ጨምሮ) ለዘርፉ የሚያቀርቡት የብድር ድርሻ ከፍ እንዲያደርጉ የሚደግፍና የሚያበረታታ ስርዓት ይዘረጋል፣
- የአምራች ኢንዱስትሪዎችን የብድር ዋስትና አይነቶች የሚያሰፋ ስርዓት ይዘረጋል፣

https://t.me/customsclearingagents ..... For More

- የፖሊሲ ተግባርን የሚወጣ የአምራች ኢንዱስትሪ ባንክ የሚያቋቁም የህግ ማዕቀፍ ይነደፋል፣ አሰራርና ተቋማዊ አደረጃጀት ይዘረጋል፣

5.2.2 ለአምራች ኢንዱስትሪ የውጪ ምንዛሪ አቅርቦት የማሳደግ አላማ

የአምራች ኢንዱስትሪው ለካፒታል ማሽንና መለዋወጫ እና ግብዓት የውጪ ግዢ የውጭ ምንዛሪ የሚፈልግ ዘርፍ ነው። መንግስት የተረጋጋ የማክሮ ኢኮኖሚ ሁኔታ በመፍጠር የአገሪቱ ኢኮኖሚ እድገት ዘላቂና ሁለን አቀፍ ሊሆን እንዲችል እንዲሁም የወጪ ንግድ ተኮር ኢንዱስትሪ ልማት ተተግብሯል። የተረጋጋ ማክሮ ኢኮኖሚ ለመፍጠር አንዱ ፖሊሲ አቅጣጫ የውጪ ምንዛሪ አቅርቦት በባንኮች ብቻ እንዲፈፀም ማድረጉ ሲሆን በተለይም የአምራች ኢንዱስትሪው በመመሪያ ደረጃ የቅድሚያ ተጠቃሚ እንዲሆን የሚፈቅድ ነው። የአምራች ኢንዱስትሪ በአብዛኛው ከውጪ በሚመጡ የማምረቻ ቴክኖሎጂዎችና ግብዓቶች ላይ የተመሠረተና የውጪ ምንዛሪ ፍላጎት ከፍተኛ እንዲሆን አድርጎታል። ይህንን ልዩ ባህሪ ከግምት ውስጥ ያስገባ የውጭ ምንዛሬ አስተዳደር መዘርጋትና ለተግባራዊነቱም የባንኮችን የውጪ ምንዛሪ አቅርቦትና አጠቃቀም መከታተልና መቆጣጠር ለአምራች ኢንዱስትሪ በቂና የተሟላ የውጪ ምንዛሪ ማቅረብ ያስችላል።

የፖሊሲው አቅጣጫ

- የአምራች ኢንዱስትሪውን ልዩ ባህሪ ባገናዘበ መልኩ የውጪ ምንዛሪ አቅርቦት ስርዓት እንዲሻሻል ይደረጋል፣
- ለአምራች ኢንዱስትሪ አማራጭ የውጪ ምንዛሪ አቅርቦት ስራ ላይ እንዲውል ይደረጋል።

የማስፈፀሚያ ስልቶች

- የአምራች ኢንዱስትሪ ልዩ ባህሪ ባገናዘበ መልኩ የውጪ ምንዛሬ አሰራር (የፖሊሲ ባንክ የውጪ ምንዛሪ የሚያገኝበትና የሚያስተዳድርበት አሰራርን ጨምሮ) ይሻሻላል፣
- ለአምራች ኢንዱስትሪ አማራጭ የውጪ ምንዛሪ አቅርቦት አሰራር (በመንግስት የዋስትና ከለላ የሚቀርቡ የውጪ ምንዛሬ አሰራር እና አለም አቀፍ የፋይናንስ ማዕከል ማቋቋምን ጨምሮ) ይዘረጋል፣

https://t.me/customsclearingagents ..... For More

5.2.3 ለአምራች ኢንዱስትሪ የመድን ሽፋን የማሳደግ አላማ

የአምራች ኢንዱስትሪው በአመራረቱ ቀልጣፋ፣ ተወዳዳሪና ትርፋማ ሆኖ ለመቀጠል በማምረቻ ፋሲሊቲዎቻቸው በሚፈጠሩ ችግሮች፣ የማምረቻ መሳሪያ ብልሽት፣ የአቅራቢ ችግር፣ የምርት ስርቆት፣ የሰራተኛ ደህንነት፣ የፖለቲካና የማክሮ ኢኮኖሚ ጉዳዮች በስጋት የታጠረ ነው። ለዚህም አስተማማኝ የመድን ሽፋን ይፈልጋል። ለአምራች ኢንዱስትሪው ከግዥት ጋር ለተያያዙ ጉዳቶች የመድን ሽፋን መዘርጋት ያስፈልጋል። በተጨማሪም የአምራቹና የሰራተኛውን ማህበራዊ ደህንነት ለማረጋገጥ የኢንሹራንስና የማህበራዊ ዋስትና አገልግሎት ማስፋፋት ያስፈልጋል።

የፖሊሲው አቅጣጫ

- የኢንሹራንስ ተቋማት ለአምራች ኢንዱስትሪው የኢንሹራንስ ሽፋን እንዲያሰፉ ድጋፍና ማበረታቻ ይደረጋል።

የማስፈፀሚያ ስልቶች

- ለአምራች ኢንዱስትሪው የኢንሹራንስ ሽፋን የሚያሰፋ አሰራር ይዘረጋል፣
- ከሰራተኞች ኢንሹራንስና የማህበራዊ ዋስትና አገልግሎት የሚገኘውን ቁጠባ ለአምራች ኢንዱስትሪ ኢንቨስትመንት ፋይናንስ የሚውልበት አሰራር ይዘረጋል፣

5.2.4 ለአምራች ኢንዱስትሪ ባንክ ያልሆኑ ሌሎች የፋይናንስ አቅርቦት የማሳደግ አላማ

ከመደበኛው የባንክ ብድር አገልግሎት አሰጣጥ ውጭ ያሉ ሌሎች የፋይናንስ አቅርቦት አይነቶች ማስፋት የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፉን በተሻለ ሁኔታ በፋይናንስ ለመደገፍ ትልቅ አማራጭ የሚፈጥር ነው። እነዚህም የረጅም ጊዜ ፋይናንስ ካፒታል ገበያ፣ የመሳሪያ ሊዝ፣ ግምጃ ቤት ሰነድ ጨምሮ ለአምራች ኢንዱስትሪዎች አማራጭ የፋይናንስ አቅርቦትን የሚያሳልጥ ፖሊሲ፣ ሬጉላቶሪ መዋቅር እና የሚመራበት የተሟላ ስርዓት መዘርጋት ያስፈልጋል። በሌላ መልኩ ከኢንሹራንስና ማህበራዊ ዋስትና የሚገኘውን ቁጠባ ለአምራች ኢንዱስትሪ አማራጭ የፋይናንስ ምንጭ ሆኖ ስጋትን ባገናዘበ መልኩ ከባንኮች ጋር ተቀናጅቶ የሚሰራበት አሠራር መዘርጋት አስፈላጊ ነው።

https://t.me/customsclearingagents ..... For More

የፖሊሲው አቅጣጫ

- ለአምራች ኢንዱስትሪ አማራጭ የፋይናንስ አቅርቦት በተለይም የረጅም ጊዜ ፋይናንስ ካፒታል ገበያ እንዲያገኙ ይደረጋል፣
- ከኢንሹራንስና ማህበራዊ ዋስትና የሚገኘውን ቁጠባ ለአምራች ኢንዱስትሪ አማራጭ የፋይናንስ ምንጭ እንዲሆኑ ይደረጋል።

የማስፈፀሚያ ስልቶች

- ለአምራች ኢንዱስትሪ አማራጭ የፋይናንስ አቅርቦት በተለይም የረጅም ጊዜ ፋይናንስ ካፒታል ገበያ (የመሳሪያ ሊዝ፣ የሼር ገበያ፣ ቬንቸር ካፒታል፣ ግምጃ ቤት ሰነድ፣ የፕሮጀክት የውጪ ፋይናንስን ጨምሮ) ስርዓት ይዘረጋል፣
- ከኢንሹራንስና ማህበራዊ ዋስትና የሚገኘውን ቁጠባ ለአምራች ኢንዱስትሪ አማራጭ የፋይናንስ ምንጭ የሚያረጋግጥ አሰራር ይዘረጋል፣

5.3. የሰው ሃይል ልማት እና አስተዳደር

የተማረ የሰው ሃይል አቅርቦት እና ምርታማ የሰው ሃይል በዘላቂነት ማረጋገጥ ለአምራች ኢንዱስትሪ ልማት ወሳኝ ሚና አለው። ይህም በዕውቀትና ክህሎት፣ በኢንዱስትሪ ባህል እና በስራ አመራር ክህሎት የዳበረ የሰው ሃይል ማቅረብ እንዲሁም የቀረበውን የሰው ሃይል መቅጠርና ምርታማነትን ማሳደግ ያካትታል።

5.3.1 ለአምራች ኢንዱስትሪ የሰው ሃይል ክህሎት የማሳደግ አላማ

የሰው ሃይል ልማት ከአምራች ኢንዱስትሪ ልማት አንፃር የተዘጋጀ ዕውቀትና ክህሎት እና የኢንዱስትሪ ባህልን የተላበሰ ሰራተኛ እንዲሁም በስራ አመራር ብቃት የተገነባ የኢንዱስትሪ አመራር ለዘላቂ የአምራች ኢንዱስትሪ ዕድገት የሚጫወተው ሚና ጉልህ ነው። በሀገራችን የቴክኒክ ክህሎትና የክህሎተ-ልቦና ስልጠና አግኝቶ በአምራች ኢንዱስትሪዎች ለመቀጠር ዝግጁ የሆኑ በቀላሉ ሊሰለጥኑ የሚችሉ ወጣቶች አሉ። ከዚህ አንጻር በነባሩ ፖሊሲ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን ማስፋፋት፣ የሙያና ቴክኒክ ስልጠና ስርዓት መዘርጋትና ማስፋፋት፣ የአምራች ኢንዱስትሪ የተከተሉ ክህሎት ማሰልጠኛ ተቋማት (የልማት ኢንስቲትዩቶች) ግንባታን ማስፋፋት፣ የስራ ላይ ልምምድ (ኢንተርንሺፕና አፕረንቲሺፕ) እና የኢንዱስትሪና የከፍተኛ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት ግንኙነትን ማጠናከር ላይ ትኩረት ያደረገ ነበር። በዚህም የአምራች

https://t.me/customsclearingagents ..... For More

ኢንዱስትሪውን በቀጥታና በተዘዋዋሪ የሚደግፉ የተለያዩ የሰው ሃይል ልማት ፖሊሲዎች፣ ደንቦችን እና ማበረታቻዎች ተዘጋጅተው ስራ ላይ ውለዋል።

የትምህርትና ስልጠና ማዕቀፎች ጥራት ያለው የሰው ሃይል ማብቃትን የሚከታተልበት አሰራር በመዘርጋት የሚቀረጹ የትምህርት ካሪኩለሞች የአምራች ኢንዱስትሪውን ፍላጎት ከግምት ውስጥ እንዲያስገቡ እንዲሁም የኢንዱስትሪ ባህል እና በተግባር የተደገፈና የስራ ፈጠራ(ኢንተርፕረነርሺፕ) ክህሎትን እንዲፈጥሩ ማድረግ ያስፈልጋል። በተጨማሪም የኢንዱስትሪ እና የከፍተኛ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት ትስስር ማበረታታት፣ የባለቤት እና የተጠያቂነት ማዕቀፍ መዘርጋት የአምራች ኢንዱስትሪው የሚፈልገውን እውቀትና ክህሎት ማቅረብ ያስችላል። በተመሳሳይ የቴክኖሎጂ ሽግግር ስልቶች ክህሎትን በሚያሳድግ መልኩ መምራት ያስፈልጋል። በሌላ መልኩ ለአምራች ኢንዱስትሪ የሚያስፈልጉ ክህሎቶች በተለይም በልምድ የዳበሩ ክህሎቶችን ደረጃና ዕውቅና የሚያረጋግጥ ስርዓት በሀገራዊ የክህሎት ማረጋገጫ ማካተት ያስፈልጋል።

የፖሊሲው አቅጣጫ

- የአምራች ኢንዱስትሪ እና የከፍተኛ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት ትስስር ጠንካራና ውጤታማ እንዲሆን ይደረጋል፣
- የከፍተኛ ትምህርት እና የስልጠና ተቋማት የሚቀረጹ ካሪኩለሞች የአምራች ኢንዱስትሪዎች የሚፈልጉትን ጥራት ያለው የሰው ሃይል በአይነትና በመጠን የሚያሟላ እና የኢንዱስትሪ ባህልን የሚያዳብሩ እንዲሆኑ ይደረጋል፣
- የአምራች ኢንዱስትሪ የቴክኖሎጂ ሽግግር እና የቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን መፈልፈያና ማበልፀጊያ ስርዓቶች ክህሎትን በሚያዳብር መልኩ እንዲጠናከሩ ይደረጋል፣
- የአምራች ኢንዱስትሪ አመራር በእውቀትና ክህሎት እንዲመራ ድጋፍና ማበረታቻ ይደረጋል።

የማስፈፀሚያ ስልቶች

- የአምራች ኢንዱስትሪ እና የከፍተኛ ትምህርትና ስልጠና ትስስር የሀገራዊ የተቋማት ትስስር የህግ ማዕቀፍ በመመርኮዝ የማስፈፀሚያ መመሪያና ስርዓት (ኢንተርንሺፕ፣ አፕረንቲሺፕ፣ ኤክስተርንሽፕ ፣ሴት ሰልጣኝና ምሩቃን

https://t.me/customsclearingagents ..... For More

ማብቃት እና ክህሎትና እውቀት ያደበሩ አምራቾች በከፍተኛ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት የሚያስተምሩብት ስርዓትን ጨምሮ) ይነደፋል፣ የማበረታቻና የተጠያቂነት አሰራር ይዘረጋል፣

- በከፍተኛ ትምህርት እና የስልጠና ተቋማት፣ በኢንዱስትሪ ምርምና ልማት ማዕከላት እና በአምራች ኢንዱስትሪ በጋራ የሚቀረጹ ካሪኩለሞች የአምራች ኢንዱስትሪ ፍላጎትን (ጥራትና መጠን) የሚያሟላ እንዲሆን የሚያስችል ስርዓት ይዘረጋል፣
- የአምራች ኢንዱስትሪ ልዩ ባህሪን ያገናዘበ የክህሎት ፖሊሲ ማዕቀፍ ይዘጋጃል፣
- የአምራች ኢንዱስትሪ የቴክኖሎጂ ሽግግር እና የቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን መፈልፈያና ማበልፀጊያ ስርዓቶች ክህሎትን በሚያዳብር መልኩ ይዘረጋል፣
- የአምራች ኢንዱስትሪ አመራር በእውቀት፣ ክህሎትና ብቃት የሚመራበት አሰራር ይዘረጋል፣

5.3.2 የአምራች ኢንዱስትሪ የሰው ሃይል አስተዳደርና ምርታማነት የማሻሻል አላማ

የአምራች ኢንዱስትሪ መስፋፋት የስራ እድል አማራጮችን በማሳደግ በፋብሪካዎች ውስጥ መስራት ከሌሎች አማራጭ ስራዎች የበለጠ ሳቢ እንደሚያደርገው ይጠበቃል። መንግስት ሰራተኛውና አሰሪው ለኢንዱስትሪ ልማት መፋጠንና በየደረጃቸው ተጠቃሚ እንዲሆኑ በጋራና በቅንጅት እንዲረባረቡ በማድረግ ረገድ ከፍተኛ የአመራር ሚና እየተጫወተ ይገኛል። ለዚህም የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ተሻሽሏል። በአምራች ኢንዱስትሪ ውስጥ ተቀጥሮ መስራት ያለውን እድልና ስጋት ከሌሎች ስራዎች ሰራተኛ ለመሳብ የሚያስፈልጉ የስልጠናና ግንዛቤ ማስጨበጫ አሰራር መዘጋት አስፈላጊ ነው። በሌላ መልኩ በስራ ላይ ያለው የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ የአምራች ኢንዱስትሪውን የሰው ሃይል ለመሳብ፣ ለማቆየትና ምርታማነትን ለማሻሻል እንዲሁም የዲሲፕሊን እርምጃዎችን ለማስፈፅም ጠንካራ አሰራር መዘርጋት ያስፈልጋል። በተጨማሪም አሰሪው የሰራተኛውን የስራ ላይ ደህንነትና ጤንነት፣ የስራ ሰዓት፣ ዝቅተኛ ክፍያን፣ የስርዓተ ፆታ በተለይም የሴት ሰራተኞች እና የህፃናት ጉልበት ብዝበዛ ጉዳዮች የሚመራበት ምቹ የስራ ከባቢ ደረጃ (ሌበር ስታንዳርድ) ማዘጋጀትና የድጋፍና ማበረታቻ ስርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ነው። ይህም የአምራች ኢንዱስትሪ የሰው

https://t.me/customsclearingagents ..... For More

ሃይል ምርታማነትን ለማሻሻል እና በዚህ ሂደት የተመረት ምርትም በአለም አቀፍ ገበያ ተቀባይነትን ያስገኛል።

የፖሊሲው አቅጣጫ

- የአምራች ኢንዱስትሪ የአሰሪና ሰራተኛ ግንኙነት ምርታማነት በሚያሳድግ መልኩ እንዲመራ ይደረጋል።

የማስፈፀሚያ ስልቶች

- የአምራች ኢንዱስትሪ የመንግስት፣ አሰሪና ሰራተኛ ግንኙነት ስርዓት (የኢንዱስትሪ አክት) ይዘጋጃል፣ ይህም የአሰሪ ጉዳዮችና ሃላፊነት እና የሰራተኛውን መብትና ግዴታ ባገናዘበ ሁኔታ የሰው ሃይል ምርታማነት በሚያበረታታ መልኩ ይዘጋጃል፣
- የአምራች ኢንዱስትሪ የካይዘን ስርዓት ይዘረጋል፣

5.4. ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን

ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን የአምራች ኢንዱስትሪውን ምርታማነትና ተወዳዳሪነት ለማሳደግ እንዲሁም ወደ ዘመናዊ ቴክኖሎጂ የምርት ስርዓት ማሻገር ወሳኝ ሚና አለው። ይህም የሀገር ውስጥ የምርምር አቅም በማሻሻል ቴክኖሎጂ መፍጠር፣ ማልማት እና ውጤታማ በሆነ መልኩ ለመጠቀም ያስችላል። በተመሳሳይ የቴክኖሎጂ ሽግግርን ማሳደግን ያካትታል።

5.4.1 የአምራች ኢንዱስትሪ ምርምርና ልማት አቅም የማሳደግ አላማ

ለሀገራችን ቴክኖሎጂ መቅዳትና ማላመድ፣ ማሻሻል፣ ማበልፀግ እና መፍጠርና ማልማት እንዲሁም ውጤታማ በሆነ መልኩ መጠቀም የሚቻለው የተጠናከረ የምርምር ስርዓት እና የሚመለከታቸው ተዋንያን የሚጠበቅባቸውን ሚና ሲጫወቱ ነው፡፡ የምርምር ተቋማት እና ከፍተኛ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት ለሳይንስና ቴክኖሎጂ መስፋፋት ዋነኛ ተዋናዮች ናቸው። በተጨማሪም አምራች ኢንዱስትሪው የምርምርና የቴክኖሎጂ ሽግግር ስራዎች በማከናወንና በመደገፍ ተግባሮች ላይ ድርሻ አላቸው። በሌላ መልኩ ፀአምራች ኢንዱስትሪው ከምርምር ተቋማት እና ከፍተኛ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት ጋር በቅርበትና በአጋርነት መስራት ይጠበቅበታል።

https://t.me/customsclearingagents ..... For More

ይህ የሚመራበት የፖሊሲ አቅጣጫ በሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ፖሊሲ ማዕቀፍ ተዘርግቷል። በተጨማሪም የአምራች ኢንዱስትሪን የሚደግፉ የምርምርና ልማት ኢንስቲትዮቶች ተቋቁመዋል። የአምራች ኢንዱስትሪ ምርምርና ልማት የሚደገፍበትና የሚመራበት የተሟላ የህግ ማዕቀፍ እና የምርምር ባህል የሚዳብርበትና የሚበረታታበት የአሰራር ስርዓት መዘርጋት ያስፈለጋል። የአምራች ኢንዱስትሪን ያማከለ የቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን መፈልፈያና ማበልፀጊያ የሚደገፍበትና የሚመራበት እንዲሁም የግል ዘርፉ በምርምርና ልማት ተሳትፎ የሚያሳድጉ አሰራሮችን ማሻሻል አስፈላጊ ነው። የአዕምሯዊ ንብረት ጥበቃ፣ የቴክኖሎጂ ባለቤትነት መብት ምዝገባና ጥበቃ እና የሮያሊቲ ክፍያ የሚመራበት ስርዓት በመዘርጋት ለአምራች ኢንዱስትሪው በቂና የተሟላ የሀገር ውስጥ ቴክኖሎጂ ኢንዲቀርብና አዳዲስ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን እንዲስፋፋ ማሻሻል ይፈልጋል።

የፖሊሲው አቅጣጫ

- የአምራች ኢንዱስትሪ የምርምና ልማት ስርዓት ሁሉን ተዋንያን አሳታፊ ባደረገ የግሉን ምርምር ተሳትፎና ውጤታማነት እንዲያሳድግ ይደረጋል፣ የምርምርና ልማት ተቋማት ውጤታማነትና ቅንጅታዊ አሰራር እንዲዘረጋ ይደረጋል፣
- የምርምርና የቴክኖሎጂ ውጤቶችን ወደ ምርትና አገልግሎት የሚሸጋገሩበት (የቴክኖሎጂ ኮሜርሻላይዜሽን) አሰራር ይጠናከራል፣
- የአምራች አንዲስትሪው በሀገር ውስጥ የሚለሙ ምርምርና የቴክኖሎጂ ውጤቶች እንዲጠቀሙ ድጋፍና ማበረታቻ ይደረጋል፣
- የአምራች ኢንዱስትሪው ከምርምር፣ የከፍተኛ ትምህርት እና ስልጠና ተቋማት ጋር የምርምርና ልማት ሥራዎችን በአጋርነት የሚያካሂዱበት አሰራር እንዲጠናከር ይደረጋል፣
- የአምራች ኢንዱስትሪን ያማከለ የቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን መፈልፈያና ማበልፀጊያ ማዕከላት እንዲፈጠሩና እንዲጠናከሩ ይደረጋል፣
- የቴክኖሎጂ ባለቤትነት መብት ምዝገባና ጥበቃ እና የሮያሊቲ ክፍያ ስርዓት እንዲጠናከር ይደረጋል።

https://t.me/customsclearingagents ..... For More

የማስፈፀሚያ ስልቶች

- የአምራች ኢንዱስትሪ የምርምና ልማት ስርዓት ይነደፋል፣ የቅንጅታዊ አሰራር ማሻሻያ ይደረጋል፣
- የአምራች ኢንዱስትሪ የግል ምርምር ምዝገባ እና ፍቃድ አሰጣጥ አሰራር እና የድጋፍና የማበረታቻ ስርዓት ይዘረጋል፣
- የአምራች ኢንዱስትሪ የቴክኖሎጂ ወደ ገበያ የማስገባት አሰራር እና የድጋፍና የማበረታቻ ስርዓት ይዘረጋል፣
- የአምራች አንዲስትሪው የሀገር ውስጥ የሚለሙ የምርምርና የቴክኖሎጂ ውጤቶች እንዲጠቀሙ ድጋፍና ማበረታቻ ስርዓት ይዘረጋል፣
- የአምራች ኢንዱስትሪው ከምርምር፣ የከፍተኛ ትምህርት እና ስልጠና ተቋማት ጋር በአጋርነት የሚሰሩበት አሰራር ይዘረጋል፣
- የአምራች ኢንዱስትሪ የቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን መፈልፈያና ማበልፀጊያ ማዕከላት ድጋፍ ስርዓት ይዘረጋል፣
- የቴክኖሎጂ ባለቤትነት መብት ምዝገባና ጥበቃ እና የሮያሊቲ ክፍያ ስርዓት ይሻሻላል፣

5.4.2 የአምራች ኢንዱስትሪ ቴክኖሎጂ ሽግግር የማሳደግ አላማ

የአምራች ኢንዱስትሪው በአለም ዓቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ እንዲሆን ከሚያስችሉት ጉዳዮች አንዱ ተስማሚ የሆነ የቴክኖሎጂ አቅርቦት ማመቻቸት እና ተጠቃሚ ማድረግ ነው። የሀገራችን ሁለንተናዊ ልማት የሚጠይቀው የቴክኖሎጂ ግብዓት በተለይ ኢንዱስትሪው በማቆጥቆጥ ላይ ያለና ጀማሪ በመሆኑ ቅድሚያ ትኩረት የተሰጠው የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ነው።። ቴክኖሎጂን ለማሸጋገር ብዙ ዓይነት መንገዶች ያሉ ቢሆንም የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት፣ የሽርክና አሰራር (ጆይንት ቬንቸር) ፣ ተርንኪ እና ቴክኖሎጂ ከውጪ ማስገባት ለዕውቀትና ቴክኖሎጂ ሽግግር ወሳኝ ሚና የሚጫወቱ ናቸው። ለዚህም የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ፖሊሲ ማዕቀፍ ተዘጋጅቷል፣ የአምራች ኢንዱስትሪን የሚደግፉ የምርምርና ልማት ኢንስቲትዩቶች ተቋቁመዋል። በተጨማሪም የኢንቨስትመንት አዋጁ የቴክኖሎጂ

https://t.me/customsclearingagents ..... For More

ሽግግር ለማሳለጥ የሽርክና አሰራሮችንም ያበረታታል። የአምራች ኢንዱስትሪ የቴክኖሎጂ ሽግግር (የቴክኖሎጂ ተቋማትን ቅንጅታዊ አሰራርን ጨምሮ) የሚደገፍበትና የሚመራበት እንዲሁም ቴክኖሎጂን ከውጪ ለማስገባትና ለመጠቀም የተሟላ አሰራር በመዘርጋት የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ማሻሻል አስፈላጊ ነው።

የፖሊሲው አቅጣጫ

- የአምራች ኢንዱስትሪ የቴክኖሎጂ ፍላጎት የመለየትና አጠቃቀሙ በቴክኖሎጂ ፍኖተ ካርታ እንዲመራ ይደረጋል፣
- የአምራች ኢንዱስትሪ የቴክኖሎጂ ሽግግር ይጠናከራል፣ የቴክኖሎጂ ተቋማት ውጤታማነትና ቅንጅታዊ አሰራር እንዲጠናከር ይደረጋል፣
- የአምራች ኢንዱስትሪ የቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ፓርክ እንዲፈጠሩና እንዲጠናከሩ ይደረጋል።

የማስፈፀሚያ ስልቶች

- የአምራች ኢንዱስትሪ የቴክኖሎጂ ፍኖተ ካርታ ይሻሻላል፣ ይህም የአምራች ኢንዱስትሪ ውጤታማ ቴክኖሎጂዎችን ለመምረጥ፣ ለማስገባት፣ ለመጠቀም፣ ለማሻሻል ፣ ለመፍጠር እንዲሁም ለማስወገድ የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፤ ውጤታማና ከሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ጋር የሚዛመዱ ቴክኖሎጂዎች ከውጭ ሀገር በሽግግር ወደ ሀገር ውስጥ ሲገቡ ዋጋና የአገልግሎት ጊዜን ለመገመት የሚያስችል ሥራ እንዲሰራ ድጋፍ ያደርጋል፤
- ለአምራች ኢንዱስትሪ የቴክኖሎጂ ሽግግር ስርዓት ይዘረጋል፣
- የአምራች ኢንዱስትሪ የቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ፓርክ ድጋፍ አሰራር ስርዓት ይዘረጋል፣
- የአምራች ኢንዱስትሪ የቴክኖሎጂ መረጃና እዉቀት አስተዳደር ስርዓት ይዘረጋል፤

5.4.3 የአምራች ኢንዱስትሪ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂና ኢመርጂንግ ቴክኖሎጂ አጠቃቀም የማሳደግ አላማ

የአምራች ኢንዱስትሪ ልማት ተወዳዳሪ ሆኖ እንዲቀጥል የቴክኖሎጂ እድገትና አጠቃቀምን ለማሳደግ ዘመናዊ የሆኑ የመገናኛ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂዎችን

https://t.me/customsclearingagents ..... For More

በመጠቀም አቅም መገንባት አስፈላጊ ነው። ሆኖም ግን የአምራች ኢንዱስትሪ በአለም ገበያ ውስጥ በዋጋና በጥራት ተወዳዳሪ ለመሆን የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂን እንዲጠቀም የሚያበረታታና የሚያስተዳድርበት ስርዓት በተሟላ መልኩ አልተዘረጋም። በዚህም ምክንያት የአምራች ኢንዱስትሪ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አጠቃቀም ዝቅተኛ ደረጃ ላይ አስቀምጦታል። ይህም የምርት ተወዳዳሪነት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ፈጥሯል። በሌላ መልኩ የኢመርጂንግ ቴክኖሎጂ ላደጉም ይሁን በማደግ ላይ ላሉ ሀገራት እኩል ዕድል የሚሰጥባቸው ሁኔታዎች በስፋት ይታያል። እነዚህም ባዮ ቴክኖሎጂ፣ ናኖ ቴክኖሎጂ፣ ማቴሪያል ሳይንስ እንዲሁም ሰው ሰራሽ አስተውሎት (አርቴፊሻል ኢንቴለጀንስ) እና የመሳሳሉት ናቸው። በሀገራችን በዚህ ዘርፍ ብዙ አቅም ቢኖርም በአግባቡ አልተጠቀምንም።

የፖሊሲው አቅጣጫ

- በተመረጡ አምራች ኢንዱስትሪ የሶስተኛው የኢንዱስትሪ አብዮት ላይ በመመርኮዝ ወደ አራተኛ አብዮት እንዲሻገር የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂን እና ኢመርጂንግ ቴክኖሎጂ እንዲጠቀሙ ድጋፍና ማበረታቻ ይደረጋል። ይህም ከሀገራዊ የአርተፊሻል ኢንተሊጀንስ የፖሊሲ ማዕቀፍ ጋር የተጣጣመ እና ለሰው ሃይል አጠቃቀምና ማህበራዊ አካታችነት ትኩረት እንዲያደርግ ይደረጋል።

የማስፈፀሚያ ስልቶች

- የአምራች ኢንዱስትሪ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂን አጠቃቀምና አስተዳደር የማበረታቻና ድጋፍ ስርዓት ይዘረጋል፣
- የአምራች ኢንዱስትሪ የኢመርጂንግ ቴክኖሎጂ አጠቃቀምና አስተዳደር የማበረታቻና ድጋፍ ስርዓት ይዘረጋል፣

5.5. ምርት ልማትና ተወዳዳሪነት

የአምራች ኢንዱስትሪ ምርት ተወዳዳሪነት ማሳደግ የኢንዱስትሪ ልማት ዋና አቅጣጫ ሲሆን ይህንን አቅም በመፍጠርም ምርቱ በሀገርና በአለምአቀፍ ገበያ ውስጥ በዘላቂነት የመቆየት አቅሙ እንዲዳብር ያደርገዋል። በመሆኑም የሀገራችን ኢንዱስትሪ ልማት ምርትን መሰረት ያደረገ የኢንዱስትሪ ክላስተር አሰራር የተከተለ፣ በተጠናከረ የግብዓት ምርት ልማት ትስስር የሚደገፍ ፣ ለወጪ ንግድና ለተኪ ምርት ልማትና

https://t.me/customsclearingagents ..... For More

ግብይት እንዲሁም ለምርት ጥራት ስራ አመራር ትኩረት የሚሰጥ ሆኖ መመራት ይኖርበታል፡፡

5.5.1 ምርትን መሰረት ያደረገ ኢንዱስትሪ ክላስተር አሰራር የመዘርጋት አላማ

የአምራች ኢንዱስትሪ ምርት መሰረት አድርጎ በተቀራራቢ አካባቢ በማሰባሰብ ማልማት የግብዓት ምርት ትስስር ለመፍጠር፣ የሰው ሃይል ለመጠቀም፣ ለገበያ ተደራሽ ለመሆን እንዲሁም የቴክኖሎጂና እውቀት ሽግግር ለማሳለጥ ይረዳል። ይህንን በመገንዘብ መንግስት የኢንዱስትሪ ዞን፣ የኢንዱስትሪ መንደር፣ የኢንዱስትሪ ፓርክ፣ የተቀናጀ የአግሮአንዱስትሪ ፓርክ እና የጥቃቅንና አነስተኛ ሼድ ግንባታዎች በማከናወን የኢንዱስትሪ ክላስተር ስርዓት ለመዘርጋት ጥረት አድርጓል። በክላስተር ውስጥ እና ከዚያ ውጭም ያሉ የአምራች ኢንዱስትሪዎች የሚመጋገቡበትና የሚተሳሰሩበት ስርዓት ማጠናከር ያስፈልጋል። በዚህም ግብዓትና ምርት ግብይት ስርዓቱን ተከትለው በተፈጥሮ የመልማት ፀጋ ላይ የተመሰረተ የኢንዱስትሪ ልማት በተለይም በኢንዱስትሪ ክላስተር የተሰባሰቡ የአምራች ኢንዱስትሪዎች የሚደገፉበት ስርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ነው። ይህም ኦርጋኒክ ክላስተሮችን በማስፋፋት ወደ ተመራጭ (አንከር) ኢንዱስትሪዎች እንዲሻገሩ ያደርጋል።

የፖሊሲው አቅጣጫ

- የአምራች ኢንዱስትሪ ልማት በኢንዱስትሪ ክላስተር ስርዓት እንዲመራ ይደገፋል። ይህም ከኢንዱስትሪ ማፕ ጋር የተናበበ ሆኖ ይመራል።
- የአምራች ኢንዱስትሪ ክላስተር የአካባቢውን የተፈጥሮ ሃብት መሰረት ያደረገ ስትራቴጂክ ምርት ተኮር እንዲሆን ይደረጋል። ምርቱም መሪና ተመራጭ ኢንዱስትሪዎችን እንዲሁም ተወዳዳሪነትን እንዲያገናዝብ ይደረጋል።
- የአምራች ኢንዱስትሪ ክላስተር የተፈጥሮ ክላስተሮች የሚያሳድግና የሚያሳትፍ ሆኖ እንዲመራ ይደረጋል።

የማስፈፀሚያ ስልቶች

- የአምራች ኢንዱስትሪ ምርት ፍኖተ ካርታ ይዘጋጃል፣
- የአምራች ኢንዱስትሪ ክላስተር አሰራር ይዘረጋል፣

https://t.me/customsclearingagents ..... For More

5.5.2 የአምራች ኢንዱስትሪ የግብዓት ምርት ትስስር የማረጋገጥ አላማ

ተወዳዳሪ የአምራች ኢንዱስትሪ ለመገንባት በሀገር ውስጥ ግብዓት ልማትና አቅርቦት ጋር የጎልዮሽና የፊትዮሽ ትስስር ከፍተኛ አስተዋጸ ያበረክታል። ይህም እሴት ሰንሰለትን መሠረት ያደረጉ የመጀመሪያ ደረጃ ምርት ልማት (በተለይም የግብርናና የማዕድን) እንዲሁም ተመጋጋቢ አምራች ኢንዱስትሪዎች ልማት እንዲስፋፉ ለማድረግ አሰራሮችን በመቀየስና የማበረታቻ ሥልቶችን በመንደፍ የግብዓት ምርት ልማትና ኢንዱስትሪ ትስስር ማሳደግ እጅግ በጣም መሠረታዊ ተግባር መሆን ይኖርበታል።

መንግስት የግብርና መር ኢንዱስትሪ ልማት ፖሊሲን በመከተል በግብርና ልማት የሚፈጠረውን ተጨማሪ የምርት እድገት በተወዳዳሪ ዋጋና መጠን የሚቀርብበትን ዕድል በመጠቀም ኢንዱስትሪው ይህንን ምርት እሴት በመጨመር የሚያመርትበት የግብዓት ምርት ትስስር የማጠናከር አቅጣጫን ተከትሏል። የአምራች ኢንዱስትሪ እና የግብዓት ምርት አቅርቦት ልማትና ትስስር የተሟላ የድጋፍና የማበረታቻ ስርዓት መዘርጋት ያስፈልጋል። በተለይም የግብርና ምርት እድገት ለአምራች ኢንዱስትሪ ግብዓት ፍላጎት መሰረት አድርጎ መምራት ይፈለጋል፣ በተመሳሳይ ለአምራች ኢንዱስትሪ ግብዓት የሚሆኑ ማዕድናት (ለአብነትም ላይምስቶን፣ የድንጋይ ከሰል፣ ፖታሽና ተፈጥሮ ጋዝ፣ አይረን ኦር/ብረት/፣ ሴራምክስ ግብዓቶች፣ ማርብልና ግራናይት) ማልማትና ማበልፀግ የሚችል የተሟላ ስርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ነው። በሌላ መልኩ በአምራች ኢንዱስትሪው መካከል እሴት የተጨመረበትን ምርት ግብዓት ልማትና ትስስር አሰራር ማሳደግ ያስፈልጋል። በዚህም ለአምራች ኢንዱስትሪው በቂ የሀገር ውስጥ ግብዓት በማቅረብ ዝቅተኛ የማምረት አቅም አጠቃቀም ማሳደግ እና ከውጪ ከሚገቡ ግብዓቶች ጥገኝነት ማላቀቅ ያስችላል።

የፖሊሲው አቅጣጫ

- በአምራች ኢንዱስትሪውና የመጀመሪያ ደረጃ ግብዓት አቅራቢ ዘርፎች (ግብርናና ማዕድን) እንዲሁም በአምራች ኢንዱስትሪዎች መካከል የግብዓት ምርት ትስስር የታሪፍ ከለላዎች ማሻሻያ እና ድጋፍና የማበረታቻ ስርዓት እንዲጠናከር ይደረጋል፣

https://t.me/customsclearingagents ..... For More

- የአምራች ኢንዱስትሪ የሀገር ውስጥ ግብዓት አጠቃቀም ምጣኔ የተዘዋዋሪ የወጪ ንግድን በሚያበረታታ መልኩ እንዲመራ ይደረጋል፣ ይህም ምርትን መሰረት ያደረገ ከኢንዱስትሪ ክላስተር አሰራር ጋር ያቀናጀ፣ ውጤታማና ተጠያቂነት የሰፈነበት የግብዓት ምርት ትስስር ስርዓት እና የተቀናጀ መዋቅራዊ አደረጃጀት ይጠናከራል።

የማስፈፀሚያ ስልቶች

- የአምራች ኢንዱስትሪ የግብዓት ምርት ትስስር ስትራቴጂ እና የልማት ፕሮግራም ይዘረጋል፣ የአሰራርና ስርዓት ይዘረጋል፣ የማበረታቻ ስርዓት ይሻሻላል፣ የመሰረተ ልማትና ሎጂስቲክስ አቅርቦት ይዘረጋል፣
- የሀገር ውስጥ ግብዓት አጠቃቀም ምጣኔ (local content) የተዘዋዋሪ የወጪ ንግድን በሚያበረታታ መልኩ በአምራች አንዱስትሪ ምርት መሰረት በማድረግ ይዘጋጃል፣ የተቀናጀ መዋቅራዊ አደረጃጀት ይዘረጋል፣

5.5.3 የአምራች ኢንዱስትሪ የወጪ ንግድ ማሳደግ

የአምራች ኢንዱስትሪው የወጪ ንግድ አመቺ የሆነ ጂኦግራፊያዊ አቀማመጥ እና ከቀረጥና ኮታ ነጻ የገበያ ዕድሎች አሟጦ በመጠቀም በግብርና ላይ ተንጠልጥሎ የሚገኘውን የሀገራዊ የውጭ ምንዛሬ ግኝት ድርሻ ለማሳደግ እንዲሁም የተወዳዳሪነትና ምርታማነትን ዘላቂነት ለማረጋገጥ ወሳኝ ሚና አለው። ይህንን በመገንዘብ መንግስት በነባሩ ፖሊሲ አቅጣጫ የወጪ ንግድ ተኮር የኢንዱስትሪ ልማት አቅጣጫን ተከትሏል። ለዚህም የወጪ ንግድ ማስፋፊያ ስትራቴጂ እና ማበረታቻ ስርዓት ተዘርግቷል። በውጭ ገበያ በሰፊው ለመሰማራትና የውጭ ምንዛሬን ለማሳደግ የሚረዱ ትላልቅ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ተገንብተዋል። የአምራች ኢንዱስትሪ ልዩ ባህሪያትን ያገናዘበ እና ትኩረት ያደረገ የተሟላ የወጪ ንግድ ማስፋፊያ ስርዓት (በተለይም ውጤታማና ተጠያቂነት ያለው ተቋማዊ ቅንጅታዊ አሰራር) መዘርጋት እንዲሁም የወጪ ንግድ ማስፋፊያና ማበረታቻ ስርዓቶች ምርታማነት፣ ጥራትና ተወዳዳሪነትን በመደገፍ የአምራች ኢንዱስትሪው የወጪ ንግድ አፈፃፀም ማሻሻል ያስችላል።

https://t.me/customsclearingagents ..... For More

የፖሊሲው አቅጣጫ

- የአምራች ኢንዱስትሪ የወጪ ንግድ አቅም ለመፍጠር በሚያግዝ መልኩ አምራቾቹ ያመረቷቸውን ምርቶች በማሰባሰብ ወደ ውጪ የሚልኩበት ስርዓት (በገበያ የተመራ የአምራች የወጪ ንግድ ኮንሶርቲየም ማቋቋምን ጨምሮ) እንዲኖር ይደረጋል፣
- የአምራች ኢንዱስትሪ ልዩ ባህሪያትን ያገናዘበ የወጪ ንግድ ማስፋፊያ ስርዓት (ውጤታማና ተጠያቂነት ያለው የተቋማት ቅንጅታዊ አሰራር ጨምሮ) እንዲኖር ይደረጋል፣
- የአምራች ኢንዱስትሪ የወጪ ንግድ የጎረቤትና አህጉራዊ አገሮችን የምርት እሴት ሰንሰለት መሰረት ያደረገ የአለም አቀፍ ተወዳዳሪነትን የሚያጎለብት አስቻይ ሁኔታዎች እንዲፈጠሩ ይደረጋል።

የማስፈፀሚያ ስልቶች

- የአምራች ኢንዱስትሪ የወጪ ንግድ ምርቶች ልማትና ግብይት ስትራቴጂ ይነደፋል፣ የማበረታቻ ስርዓት ይሻሻላል፣ የተቀናጀ መዋቅራዊ አደረጃጀት ይዘረጋል፣
- የአምራች ኢንዱስትሪ የወጪ ንግድ የጎረቤትና አህጉራዊ አገሮችን የምርት እሴት ሰንሰለት መሰረት ያደረገ የአለም አቀፍ ተወዳዳሪነት የሚያሳድግ ስትራቴጂ፣ የህግ ማእቀፍና አሰራር ይዘረጋል፣

5.5.4 ከውጪ የሚገቡ የአምራች ኢንዱስትሪ ምርቶችን በሀገር ውስጥ ምርት የመተካት አላማ

የተለያዩ ሀገራት ልምድ እንደሚያሳየው የኢንዱስትሪ መሰረትን ለማስፋት፣ የሀገር ውስጥ ፍላጎትን በጥራትና ተወዳዳሪነት ለማሟላት ብሎም በዘላቂነት ምርቱን ለውጭ ገበያ የሚያቀርብ ጠንካራና ተወዳዳሪ ኢንዱስትሪ መገንባት የቻሉት ገቢ ምርት የሚተኩ ኢንዱስትሪ ላይ አተኩረው በሰሩት ስራ ነው። የውጪ ንግድ ከማስፋፋት ጎን ለጎን በተመረጡ ምርቶች ላይ ባተኮረና አዋጭ በሆኑ መልኩ በቂ አቅም ባለባቸው ቦታዎች የተኪ ምርት ስርዓትን መከተል ያስፈልጋል። ይህም ለወጪ ንግድ ምርት ግብዓት የሚያገለግሉ እና ከፍተኛ የተኪ ምርት አቅም ያላቸው የመጨረሻ ምርቶችን

https://t.me/customsclearingagents ..... For More

ያካተተ ነው። ከውጪ የሚገቡ ምርቶችን በሀገር ውስጥ ምርት መተካት አምራቾችን የሚደግፍ የተሟላ የድጋፍና የማበረታቻ ስርዓት መዘርጋት ይፈልጋል። ይህም ለሀገር ውስጥ ፍጆታ የሚመረቱ ምርቶች ከውጪ በሀጋዊና ህጋዊ ባልሆነ መልኩ የሚገቡ ደረጃቸውን ያልጠበቁ ምርቶች ጋር የታሪፍ ከለላ ማድረግ አስፈላጊ ነው።

የፖሊሲው አቅጣጫ

- ከውጪ የሚገቡ የአምራች ኢንዱስትሪ የተመረጡ ምርቶችን በሀገር ውስጥ ምርት ለመተካት ድጋፍና ማበረታቻ ይደረጋል፣ የምርት ተወዳዳሪነት እንዲረጋገጥ ይደረጋል፣ የምርት ግብይት ስርዓት ይጠናከራል፣ ከውጪ የሚገቡ ምርቶች ህጋዊነት እና የታሪፍ ከለላዎች ይጠበቃል፤ እንዲሁም የሀገር ውስጥ ምርትን የማስተዋወቅና የማስፋፋት ስራዎች ይጠናከራሉ።

የማስፈፀሚያ ስልቶች

- ከውጪ የሚገቡ የአምራች ኢንዱስትሪ ምርቶችን በሀገር ውስጥ ምርት ለመተካት በተመረጡ የተወዳዳሪ ምርቶች እሴት ሰንሰለት ስትራቴጂ ይነደፋል፣ የድጋፍና የማበረታቻ ስርዓት ይዘረጋል፣
- የሀገር ውስጥ ምርት የማስተዋወቅና የማስፋፋት ስርዓት (የመንግስት ግዥን ማበረታታት ጨምሮ) ይሻሻላል፣ መዋቅራዊ አደረጃጀት ይገነባል፣

5.5.5 የአምራች ኢንዱስትሪ የምርት ጥራት ስራ አመራር ስርዓት የማጠናከር አላማ

የአምራች ኢንዱስትሪው በተለይም በውጭ ገበያ ተወዳዳሪ እንዲሆን ገበያው የሚፈልገውን ደረጃ ለማሟላት የምርት ጥራቱን በዘላቂነት ማሻሻል ይኖርበታል። በተመሳሳይም በሀገር ውስጥ የሚመረቱ ምርቶችን ለማሳደግ ከውጭ የሚገቡ ምርቶች የሚፈለገውን የጥራት ደረጃ እንዲያሟሉ እና ተገቢ ዋጋ እንዲኖራቸው ማረጋገጥ ያስፈልጋል። የአምራች ኢንዱስትሪ ምርትን ተወዳዳሪነት ለማረጋገጥ የብሄራዊ የጥራት መሰረተ ልማቶች፣ የኢትዮጵያ ጥራት ሽልማት፣ የካይዘን ልህቀት ማዕከል፣ የኢንዱስትሪ ምርምርና ልማት ማዕከላት፤ የምርታማነት ማሻሻያ ማዕከላት ማጠናከርና የአምራች አንዱስትሪ ምርት ጥራት ስራ አመራር ስርዓት የተሟላ የማበረታቻና የማስፈፀሚያ አሰራር መዘርጋት አስፈላጊ ነው።

https://t.me/customsclearingagents ..... For More

የፖሊሲው አቅጣጫ

- የአምራች አንዱስትሪ ምርት ጥራት ስራ አመራር ስርዓት የሚደግፍና የሚያበረታት እንዲሁም ጠንካራ የማስፈፀሚያ አሰራር እንዲኖረው ይደረጋል።

የማስፈፀሚያ ስልቶች

- የአምራች ኢንዱስትሪ ጥራት ስራ አመራር ስርዓት የድጋፍና ማበረታቻ ስርዓት ይሻሻላል፣ ተፈፃሚነቱን የሚያረጋግጥ የህግ ማዕቀፍ ይዘጋጃል፣ የተቀናጀ መዋቅራዊ አደረጃጀት ይዘረጋል፣

5.6. የአካባቢ እና ማህበራዊ አካታችነትና ዘላቂነት

የአምራች ኢንዱስትሪ ልማትን አካታችነትና ዘላቂነት ማረጋገጥ ዘርፈ ብዙ ጉዳዮች በመሆኑ ከላይ በቀረቡት ዋና ዋና ፖሊሲ ጉዳዮች ውስጥ ተካተው የሚተገበሩ ይሆናሉ። እነዚህም የአካባቢ ጉዳዮች ማካተት እና የሴቶች ተሳትፎ፣ አበርክቶና ተጠቃሚነትን ማረጋገጥን ያካትታል።

5.6.1 የአምራች ኢንዱስትሪ የአካባቢ ዘላቂነት የማሳደግ አላማ

የአምራች ኢንዱስትሪዎች የአመራረት ስልት ከአካባቢ ጋር የተዛመደ፣ የማህበረሰቡን ደህንነት የሚጠብቅ ማድረግ እንዲሁም አለምዓቀፋዊ የአካባቢ ስምምነቶች ያገናዘበ እና ሀገራዊ የአካባቢ ህጎችና መመዘኛ መስፈርቶችን ማሟላት ለዘርፉ እድገት ወሳኝ ሚና አለው። የአምራች ኢንዱስትሪ ዘላቂ የማምረት ሂደት እንዲከተል እና ግብዓት ወይም ምርት ደጋግሞ ጥቅም ላይ የሚያውል፣ ግብዓት መጠን የሚቀንስ እና ዝቅተኛ ተረፈ ምርት ያለው ሆኖ ምርታማነትን የሚያሳድግ እና የአካባቢ ብክለት የሚቀንስ ይሆናል። መንግስት የአካባቢ ፖሊሲ ማእቀፍ እና ለአየር ንብረት የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ስትራቴጂ ተተግብሮ ዘላቂ የአምራች ኢንዱስትሪ ልማት የሚደግፍና የሚያበረታታ ስርዓት ተዘርግቷል። የአምራች አንዱስትሪ ሰርኩላር ምርት ስርዓትን (ዘላቂና አረንጓዴ ማምረት ሂደትን ጨምሮ) ለማሳደግ የተሟላ ድጋፍና ማበረታቻ እና የማስፈፀሚያ አሰራር እንዲሁም የተቀናጀ ተቋማዊ አደረጃጀት መፍጠር አስፈላጊ ነው።

https://t.me/customsclearingagents ..... For More

የፖሊሲው አቅጣጫ

- የአምራች አንዱስትሪ የሰርኩላር ምርት ስርዓትን የሚደግፍና የሚያበረታት እንዲሁም ጠንካራ የማስፈፀሚያ አሰራር እንዲኖረው ይደረጋል።

የማስፈፀሚያ ስልቶች

- የአምራች ኢንዱስትሪ ሰርኩላር ምርት ስርዓትን የድጋፍና ማበረታቻ ስርዓት ይሻሻላል፣ ተፈፃሚነቱን የሚያረጋግጥ የህግ ማዕቀፍ ይሻሻላል፣ የተቀናጀ መዋቅራዊ አደረጃጀት ይዘረጋል፣

5.6.2 በአምራች ኢንዱስትሪ የሴቶች ተሳትፎ፣ አበርክቶ እና ተጠቃሚነት የማረጋገጥ አላማ

በህገ-መንግስቱ አንቀፅ 35 ሴቶች በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊ እና በፖለቲካው ዘርፍ በሚደረጉ ማናቸውም እንቅስቃሴዎች ከወንድ እኩል መብት እንዳላቸው በግልፅ ያስቀምጣል። እነዚህን የህገ-መንግስት ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ መንግስት ሁለንተናዊ የሴቶችን ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የሴቶች ፖሊሲ እና የሴቶች የልማትና የለውጥ ስትራቴጂ ተዘጋጅተው በሥራ ላይ ውለዋል፣ ማሻሻያዎችን አድርጓል በዚህም በተለይም በአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ሴቶች ከኢንዱስትሪ ባለቤትነት እስከ ቋሚ የስራ ተቀጣሪነት ድረስ ያላቸዉ ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት እንዲጨምር ምቹ ሁኔታ ፈጥሯል። በተጨማሪም የሴቶች ጉዳይ በልማት ዕቅዶች ውስጥ በባለ ብዙ ዘርፍ ውስጥ እንዲካተት ተደርጓል። የአምራች አንዱስትሪ የሴቶች ተሳትፎ፣ አበርክቶ እና ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ የፋይናንስ፣ የውጭ ምንዛሬ፣ የመሬት፣ የሃይል እና የቴክኖሎጂ አቅርቦት በተለየ የሚደግፍና የሚያበረታታ የማስፈፀሚያ አሰራር መዘርጋት አስፈላጊ ነው። ይህም ሴቶችን በአምራች ኢንዱስትሪ ውስጥ ለመሳብና ለመደገፍ አስቻይ ሁኔታዎች በበቂ ሁኔታ ማበረታታት የሴቶች ተሳትፎ፣ አበርክቶ እና ተጠቃሚነት እንዲሁም የባለቤትነትና አመራር ሰጪነት ድርሻም ለማሳደግ ወሳኝ ሚና አለው።

የፖሊሲው አቅጣጫ

- የአምራች አንዱስትሪ የሴቶች ተሳትፎ፣ አበርክቶ እና ተጠቃሚነት የሚደግፍና የሚያበረታታ እንዲሁም ጠንካራ የማስፈፀሚያ አሰራር እንዲኖረው ይደረጋል፣

https://t.me/customsclearingagents ..... For More

- የሴት አምራቾች የመሬት አቅርቦት፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን አጠቃቀም፣ ፋይናንስ አገልግሎት፣ የምርት ጥራትና ተወዳዳሪነት እንዲሁም ገበያ ትስስር እንዲጠናከር ይደረጋል።

የማስፈፀሚያ ስልቶች

- የአምራች አንዱስትሪ የሴቶች ተሳትፎ፣ አበርክቶ እና ተጠቃሚነት የድጋፍና ማበረታቻ ስርዓት ይሻሻላል፣ ተፈፃሚነቱን የሚያረጋግጥ የህግ ማዕቀፍ ይዘጋጃል፣ የተቀናጀ መዋቅራዊ አደረጃጀት ይዘረጋል፣ ፣
- ተቋማዊ የሆነ ስርዓተ ፆታን ያማከለ በሁሉም አካላት የሚከናወን የዕቅድ፣ ትግበራ፣ ክትትል፣ ቁጥጥር እና ሪፖርት ስርዓት ይዘረጋል፣
- ስርዓተ ፆታን ያማከለ እና አካታች የሆነ የተዋረድና የጎንዮሽ የአሰራር ቅንጅትና የትብብር የማትጊያና ተጠያቂነት (ውጤታማነት መከታተያ) ስርዓት ይዘረጋል፣

5.6.3 በአምራች ኢንዱስትሪ የወጣቶች ተሳትፎ፣ አበርክቶ እና ተጠቃሚነት የማረጋገጥ አላማ

መንግስት ሁለንተናዊ የወጣቶች ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የፖሊሲ አቅጣጫዎች ዘርግቷል፣ ማሻሻያዎችን አድርጓል በዚህም በተለይም በአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ወጣቶች በጥቃቅን፣ አነስተኛና መካከለኛ አምራች ኢንዱስትሪ ባለቤትነት እንዲሁም በከፍተኛ ኢንዱስትሪ ውስጥ ቋሚ የስራ ተቀጣሪነት ያላቸዉ ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት እንዲጨምር ምቹ ሁኔታ ፈጥሯል። የአምራች አንዱስትሪ የወጣቶች አዲስ ፈጠራ የሚደግፍና የሚያበረታታ አሰራር በተለይም አዲስ የፈጠራ ሃሳብ የፋይናንስ አቅርቦት ማሳደግ ወሳኝ ነው። በተጨማሪም የአምራች አንዱስትሪ የወጣቶች ተሳትፎ የክትትልና ማስፈፀሚያ አሰራር በመዘርጋት ወጣቶችን በአምራች ኢንዱስትሪ ውስጥ ለመሳብና ለመደገፍ አስቻይ ሁኔታዎችን በማመቻቸት የሚጠበቅበትን ተሳትፎ፣ አበርክቶ እና ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

የፖሊሰው አቅጣጫ

- የአምራች አንዱስትሪ የወጣቶች ተሳትፎ፣ አበርክቶ እና ተጠቃሚነት የሚደግፍና የሚያበረታታ እንዲሁም ጠንካራ የማስፈፀሚያ አሰራር እንዲኖረው ይደረጋል።

https://t.me/customsclearingagents ..... For More

- ወጣት አምራቾች የመሬት አቅርቦት፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ፈጠራና አጠቃቀም፣ ፋይናንስ አገልግሎት፣ የምርት ጥራትና ተወዳዳሪነት እንዲሁም ገበያ ትስስር እንዲጠናከር ይደረጋል።

የማስፈፀሚያ ስልቶች

- የአምራች አንዱስትሪ የወጣቶች ተሳትፎ፣ አበርክቶ እና ተጠቃሚነት የድጋፍና ማበረታቻ ስርዓት ይሻሻላል፣ ተፈፃሚነቱን የሚያረጋግጥ የፖሊሲ ማዕቀፍ ይዘጋጃል፣ የተቀናጀ መዋቅራዊ አደረጃጀት ይዘረጋል፣

6. የፖሊሲው አፈፃፀም ማዕቀፍ

ይህን ሀገራዊ የአምራች ኢንዱስትሪ ፖሊሲ ትግበራ ለመምራት፣ ለመደገፍና ለመከታተል በሚያስችል ሁኔታ የፖሊሲ አፈፃፀም ማዕቀፍ ይዘጋጃል። ይህም ከላይ በቀረቡት ዋና ዋና የፖሊሲ ጉዳዮች ስር በተዘረዘሩት የፖሊሲ ማስፈፀሚያ ስልቶች ማለትም ራሳቸውን የቻሉ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች/ፍኖተ ካርታ፣ የህግ ማዕቀፎች፣ አሰራሮች እና ተቋማዊ አደረጃጀቶች መሰረት በአጭር፣ መካከለኛ እና በረጅም ጊዜ ተቀርፀው ወይም ተዘርግተው ይተገበራሉ። ለፖሊሲው ትግበራ የሚያስፈልገው የፋይናንስና ሌሎች ድጋፍ ስርዓቶች ይዘጋጃሉ።

7. ፖሊሲውን የማስፈፀም ኃላፊነት ያለባቸው ተቋማት

ይህንን ሀገራዊው የአምራች ኢንዱስትሪ ፖሊሲ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ ኃላፊነት ያለባቸው ተቋማት የሚለይ እና በመካከላቸው የሚያስፈልግውን ትብብርና ቅንጅት የሚመራበት የፖሊሲ አስተዳደር ስርዓት ይዘረጋል። ይህም ከፌዴራል ጀምሮ እስከታችኛው የአስተዳደር እርከን ድረስ የሚዘረጋ ሆኖ ዋና ዋና ተዋናዮችም መንግስት፣ የአምራች ኢንዱስሪ ምክር ቤት፣ አምራች የግሉ ዘርፍ እና ሌሎች ተዋናዮችና ባለድርሻ አካላት ያካትታል።

የመንግስት ሚና በዋናነት ፖሊሲ መቅረፅ፣ ምቹ የቢዝነስ ምህዳር መፍጠር፣ የተለያዩ የአደረጃጀት እና የአሠራርና ዲጂታል ሥርዓቶችን በመዘርጋት የዘርፉን የቁጥጥርና አስተዳደራዊ አገልግሎቶችን ያቀርባል። እንደአስፈላጊነቱ በግሉ ዘርፍ በአጥጋቢ ሁኔታ ሊሰሩ የማይችሉትን የአምራች ኢንዱስትሪ ምርት ማምረት ሂደት

https://t.me/customsclearingagents ..... For More

ውስጥ በተመረጠ ሁኔታ እና አዋጪነቱን በጠበቀ መንገድ የገበያ ጉድለቱን ለመሙላት ይሳተፋል።

ይህንን ፖሊሲ ለማስፈፀም የበርካታ የፌዴራል እና የክልል ተቋማትን ሚናና ሃላፊነት የሚጠይቅ ሲሆን የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር እና የክልል ኢንዱስትሪ ቢሮዎች የአምራች ኢንዱስትሪ ልማት ተግባራትን በዋናነት ይተገብራሉ፣ ያስተባብራሉ። በተጨማሪም የአምራች ኢንዱስትሪ ልማት ከኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ተግባርና ሃላፊነት ተሻጋሪ በመሆኑ ዘርፈ-ብዙ ባለድርሻ አካላትን የሚያሳትፍ እና በመንግስት ከፍተኛ ውሳኔ ሰጪ አካል የሚመራ የአምራች ኢንዱስትሪ ምክር ቤት ይቋቋማል። ምክር ቤቱ የአምራች ኢንዱስትሪ ልማትን በተናበበና በተቀናጀ መልኩ ይመራል፣ የፖሊሲውን አፈፃፀምና ውጤታማነት ይመራል፣ ይከታተላል፣ ይገመግማል፣ ውሳኔ እና አቅጣጫዎችን ይሰጣል። የግሉ ዘርፍ በአምራች ኢንዱስትሪ ልማት ውስጥ ዋና ተዋናይ ወይም መሪ ይሆናል፣ የኢትዮጵያ አምራች ኢንዱስትሪዎች ማህበር በማጠናከር በፖሊሲ ቀረፃና ማፅደቅ፣ ክትትልና ግምገማ ላይ ንቁ ተሳታፊ ይሆናሉ። ሌሎች ተዋናዮችና ባለድርሻ አካላት በአምራች ኢንዱስትሪ ልማት ውስጥ ጉልህ ሚና በሚጫወቱበት መልኩ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ይደረጋል።

8. የፖሊሲ ክትትል፣ የግምገማ እና የክለሳ ስርዓት

የፖሊሲውን ትግበራ ለመከታተል እና ውጤታማነቱን ለመለካት ጠንካራ የክትትል፣ ግምገማና የመማር ሥርዓት ይዘረጋል። በተጨማሪም የተመረጡ የፖሊሲ አቅጣጫዎች በሰፊው ስራ ላይ ከመዋላቸው በፊት በሙከራ ሲተገበሩ የተጠናከረ መረጃ የማሰባሰብና የትንተና ስርዓት ይዘረጋል። በዚህ ላይ በመመርኮዝ ፖሊሲው እንደ አስፈላጊነቱ እንዲከለስ ይደረጋል።

9. የፖሊሲው ስርጭት

የፀደቀው የፖሊሲ ሰነድ በህትመትና ሌሎች የመገናኛ ዘዴዎችን በመጠቀም ለባለድርሻ አካላት እንዲደርስ ይደረጋል።

https://t.me/customsclearingagents ..... For More

10. ፖሊሲው ተፈጻሚ የሚሆንበት ጊዜ

ፖሊሲው በሚኒስትሮች ምክር ቤት ቀርቦ ከፀደቀበት _____ ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

https://t.me/customsclearingagents ..... For More

11. የቃላት መፍቻ